የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አስራሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፮
አዲስ አበባ - ግንቦት ፳፬ ቀን ፲፱፻፺፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

13th Year No. 46
ADDIS ABABA-1st June, 2007

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፴፯/፲፱፻፺፱
የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች የጥበቃ አባሎች መተዳደሪያ
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ..............ገጽ፫ሺ፮፻፹፭

## CONTENTS

Council of Ministers Regulations No. 137/2007
Federal Prison Wardens Administration Council of Ministers Regulations .................. Page 3685

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፴፯/፲፱፻፺፱ ስለፌዴራል ማረሚያ ቤቶች የጥበቃ አባላት አስተዳደር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፯ አንቀጽ ፭ እና በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፭/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፴፱ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች የጥበቃ አባሎች መተዳደሪያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፴፯/፲፱፻፺፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፤

፩. ‹‹አስተዳደር›› ማለት የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ነው፤

፪. ‹‹ማረሚያ ቤት››፣ ‹‹ታራሚ›› እና ‹‹የማረሚያ ጠባቂ›› የሚሉት ቃላት በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፭/፲፱፻፺፭ የተሰጣቸው ትርጉም ይኖራቸዋል፡፡

፫. ‹‹ፍርድ ቤት›› ማለት የፌዴራል ፍርድ ቤት ወይም የፌዴራል ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን የተሰጠው ፍርድ ቤት ነው፤

፬. ‹‹የሕክምና ተቋም›› ማለት በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ሥር የሚገኝ የሕክምና ተቋም ወይም ለማረሚያ ጥበቃ አባላትና ለታራሚዎች የህክምና አገልግሎት የሚሰጥበት ተቋም ነው፤

ያንዱ ዋጋ 6.40
Unit Price

## Council of Ministers Regulations No. 137/2007

## THE COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO PROVIDE FOR THE ADMINISTRATION OF FEDERAL PRISON WARDENS

These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2005 and Article 39(1) of the Federal Prison Commission Establishment Proclamation No. 365/2003.

### *PART ONE*

### *GENERAL*

1. *Short Title*

These Regulations may be cited as the "Federal Prison Wardens Administration Council of Ministers Regulations No. 137/2007".

2. *Definition*

In these regulations unless the context requires otherwise:

1. "Administration" means the Federal Prison Administration;
2. the terms "prison", "prisoner" and "warden" shall have the meanings given to them under the Federal Prison Commission Establishment Proclamation No. 365/2003;
3. "court" means a federal court or a court that is entrusted with the judicial authority of a federal court;
4. "medical institution" means a health center that functions under the Administration or an institution that provides health services for prison wardens and prisoners;

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.Box 80,001

፭. «ማሠልጠኛ ተቋም» ማለት መደበኛ የማረሚያ ጥበቃ አባላት የሙያ ሥልጠና የሚሰጥበት ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት ወይም ተቋም ነው፡፡

፫. የደንቡ ተፈጻሚነት ወሰን

፩. ይህ ደንብ ዋና ዳይሬክተሩን፣ ምክትል ዋና ዳይሬክተሩንና በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት የሚተዳደሩ የአስተዳደሩን ሲቪል ሠራተኞች ሳይጨምር በማናቸውም የሥራ ደረጃ በሚገኝ የማረሚያ ጥበቃ አባል ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

፪. በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ምልመላ፣ ቅጥር፣ ሥልጠና፣ ምደባና ዝውውር

፬. የምልመላ መመዘኛዎች

፩. ማናቸውም የማረሚያ ጥበቃ አባል ለመሆን የሚፈልግ ሰው፣

ሀ/ ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ የሆነ፣

ለ/ በወንጀል የጥፋተኝነት ሪከርድ የሌለበት፣

ሐ/ ለሕገ-መንግሥቱ ተገዥ የሆነ፣

መ/ የተሟላ የጤናና የአካል ብቃት ያለው፣

ሠ/ ዕድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነ፣

ረ/ ቢያንስ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ያጠናቀቀ፣

ሰ/ መልካም ሥነ-ምግባር ያለው እና

ሸ/ የማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት አባል ያልሆነ፣

መሆን አለበት፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣

ሀ/ በመግቢያ ፈተና እኩል ውጤት ያስመዘገቡ የተለያዩ የብሔር ብሔረሰብ አባላት ቢኖሩ ዝቅተኛ የብሔር ተዋጽኦ ያላቸው አባላት፣ እና

ለ/ በውጤታቸው ከወንዶች ጋር እኩል የሆኑ የሴት ተወዳዳሪዎች፣ የቅጥር ቅድሚያ ያገኛሉ፡፡

፫. አስተዳደሩ ሴቶች እና ዝቅተኛ ተዋጽኦ ያላቸው ብሔር ብሔረሰብ አባላት የማረሚያ ጥበቃ አባላት ሆነው እንዲቀጠሩ ልዩ ጥረት ያደርጋል፡፡

፬. የማረሚያ ጥበቃ አባል የምልመላ ማስታወቂያ ሂደት አስተዳደሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይሆናል፡፡

፭. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፩ መሠረት ለጥበቃ አባልነት የተመለመለ ማንኛውም ሰው በአስተዳደሩ የሚዘጋጅ የቅጥር ውል ይፈጽማል፡፡ ቅጥሩ የሚጸናበት ጊዜ በቅጥር ውሉ ላይ ይገለጻል፡፡

፮. ማንኛውም በጥበቃ አባልነት የተቀጠረ ሰው ለሰባት ዓመት የማገልገል ግዴታ ይኖርበታል፡፡

፭. ሥልጠና

፩. ማንኛውም ለማረሚያ ጥበቃ አባልነት የተመለመለ ሰው አገልግሎት ከመጀመሩ በፊት መሠረታዊ የጥበቃ ሥልጠና ይሰጠዋል፡፡

5. "training institution" means a training school or an institution where regular professional training is given to prison wardens.

3. *Scope of Application*

1. These Regulations shall be applicable to prison wardens holding all positions with the exception of the Director General, the Deputy Director General and employees of the Administration who are administered in accordance with the federal civil service laws.
2. Provisions of this regulations set out in the masculine gender shall also apply the feminine gender.

## PART TWO

## RECRUITMENT, EMPLOYMENT, TRAINING ASSIGNMENT AND TRANSFER

4. *Recruitment Criteria*

1. Any person who wants to become a prison warden shall:
   a) be an Ethiopian Citizen;
   b) have no criminal record;
   c) be loyal to the Constitution;
   d) be healthy and have physical fitness;
   e) be above the age of 18;
   f) have completed at least high school education;
   g) have good conduct; and
   h) not be a member of any political organization.
2. Without prejudice to the provisions of sub-article (1) of this Article Priority of employment shall be given to:
   a) candidates from a nation or nationality with relatively less representation where candidates from different nations and nationalities score equal results; and
   b) female candidates who have equal results with male candidates.
3. The Administration shall make special efforts to enable women and members of a nation or nationality with less representation to be employed as prison wardens.
4. The Administration shall, by directives, determine the process of warden recruitment notice.
5. Any person recruited to be a prison warden in accordance with sub-article (1) of this Article shall sign employment contract with the Administration. The effective date of the employment shall be specified in the contract.
6. Any person employed as a prison warden shall serve for a compulsory period of seven years.

5. *Training*

1. Any prison warden shall receive basic warden training prior to his assignment to regular warden duty.

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው ሥልጠና ዓላማ ለሕገመንግሥት መከበር የሚቆም ብቃት ያለው ባለሙያ የሆነ የማረሚያ ጥበቃ አባል መፍጠር ይሆናል፡፡

፫. የሥልጠና ዓይነቶች እንደሚከተለው ይመደባሉ፤
  - ሀ/ መሠረታዊ የማረሚያ ጥበቃ አባል ሥልጠናዎች፤
  - ለ/ ከማረሚያ ጥበቃ አባል ሥራ ጋር የሚገናኙ ልዩ ልዩ የሙያ ሥልጠናዎች፣ እና
  - ሐ/ ለአመራር የሚያበቁ ሥልጠናዎች፡፡

፬. ሥልጠናዎችን ለማስፈጸም የሚያስፈልገው ዝርዝር ሁኔታ አስተዳደሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፭. ማንኛውም ሠልጣኝ በሥልጠና ወቅት፣
  - ሀ/ ምግብ፣የመኝታ አገልግሎት፣ልብስ፣ ጫማ፣ የጽሕፈት መሣሪያና የጽዳት እቃ እንዲሁም አስተዳደሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የኪስ ገንዘብ ያገኛል፤
  - ለ/ ለሚደርስበት ሕመም ነጻ ሕክምና ያገኛል፡፡

፮. <u>የሠልጣኝ ግዴታ</u>

ማንኛውም ሠልጣኝ፣

፩. በሚመደብበት የሥልጠና ፕሮግራም የመሳተፍ፣

፪. የሚገባበትን የማሰልጠኛ ተቋም ውስጠ ደንብና መመሪያ የማክበር፣

፫. የተመደበበትን የሥልጠና መስክ ለማቋረጥ፣ ለመቀየር ወይም ለማራዘም ሲፈልግ አስተዳደሩን በቅድሚያ የማስፈቀድ፣ ግዴታ አለበት፡፡

፯. <u>ቃለ መሃላ</u>

፩. ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል መሠረታዊ የጥበቃ ሥልጠና እንዳጠናቀቀ ሥራ ከመጀመሩ በፊት የሚከተለውን ቃለ መሃላ ይፈጽማል፤

"እኔ............................................ሕገ-መንግሥቱን በሚገባ ለመጠበቅ፣ መደበኛ ሥራዬን ሳከናውን በሕጉ መሠረት ልሠራ፣ በተለይ የታራሚዎችን ሰብአዊ ክብርና መብት ላከብርና ላስጠብቅ፣ በሀቀኝነትና በቅንነት ኃላፊነቴን ለመወጣት ቃል እገባለሁ፡፡"

፪. የተፈፀመው ቃለ መሃላ በማረሚያ ጥበቃ አባሉ ተፈርሞ በግል ማህደሩ ውስጥ ይቀመጣል፡፡

፰. <u>ምደባ</u>

፩. አንድ ሰልጣኝ ሥልጠናውን ከጨረሰ በኋላ በሰለጠነበት ሙያ በአስተዳደሩ ይመደባል፡፡

፪. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ቢኖርም አስተዳደሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሰልጣኙ ከሰለጠነበት ሙያ ውጭ በሆነ ሥራ ላይ ሊመድበው ይችላል፡፡

፱. <u>የውስጥ ዝውውር</u>

፩. አስተዳደሩ ለሥራው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ማንኛውንም የጥበቃ አባል በአስተዳደሩ ውስጥ ከአንድ የሥራ መደብ እኩል ደረጃ ደመወዝ ወደአለው ሌላ የሥራ መደብ ወይም ከአንድ የሥራ ቦታ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ በማዛወር ሊያሰራው ይችላል፡፡

2. The objective of the training is to create professional prison wardens dedicated to the enforcement of the Constitution.

3. The types of trainings shall be categorized as:
   a) basic warden trainings.
   b) various professional trainings related to warden services; and
   c) managerial trainings.

4. The Administration shall issue directives to determine the detailed requirements for the implementation of trainings.

5. Any recruit on a basic warden training shall be entitled to:
   a) get food, lodging, clothing, shoes, stationery, sanitation materials as well as a pocket money determined by directives of the Administration;
   b) receive free medical services for any illness.

6. *<u>Obligations of Trainees</u>*

Any trainee shall have the obligations to:

1. participate in the training program into which he is assigned;
2. observe the internal regulations and directives of the training institution into which he is admitted;
3. obtain the permission of the Administration before terminating, changing or extending his field of training.

7. *<u>Oath</u>*

1. Any prison warden who has completed basic warden training program shall, prior to commencing his work, take the following oath:

"I..____________________ swear to properly protect the Constitution, to do my regular work in accordance with the law, in particular to respect and protect the human rights and dignity of prisoners, to discharge my responsibilities with integrity and honesty."

2. The oath, after duly signed by the prison warden, shall be filed in his personal file.

8. *<u>Assignment</u>*

1. A prison warden shall be assigned by the Administration to a duty related to his training.
2. Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, the Administration may, if it finds it necessary, assign a prison warden to a duty other than that he was trained for.

9. *<u>Internal Transfer</u>*

1. The Administration may, whenever necessary, transfer a prison warden to another position of an equal grade and salary or to another place of work within the Administration.

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት በውስጥ ዝውውር ሊሞላ በሚችል ክፍት የሥራ መደብ ላይ መሥራት የሚፈልጉ ሌሎች ጥበቃ አባሎች ሲኖሩ ዝውውሩ በውድድር ይሆናል።

፫. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፩ ድንጋጌ ቢኖርም አስተዳደሩ ሥራው እንዳይበደል የአንድን የማረሚያ ጥበቃ አባል ደመወዝ ሳይቀንስ ደረጃውን ወይም የያዘውን የሥራ ዓይነት ሳይጠብቅ ከአንድ ዓመት ላልበለጠ ጊዜ በጊዜያዊነት አዛውሮ ማሠራት ይችላል።

፬. ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል በጤና መታወክ ምክንያት በያዘው የሥራ መደብ ላይ ወይም ባለበት የሥራ ቦታ ሊሠራ አለመቻሉ በሀኪም ማስረጃ ሲረጋገጥ፣

ሀ) በተመሳሳይ ደረጃ ሊመደብ የሚችልበት ክፍት የሥራ መደብ ካለ በያዘው ደረጃ፣ ወይም

ለ) በተመሳሳይ ደረጃ ሊመደብ የሚችልበት ክፍት የሥራ ቦታ ከሌለና ጥበቃ አባሉ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ለመሥራት ፈቃደኛ ከሆነ ደረጃው ተቀንሶ ወደሚስማማው የሥራ መደብ ወይም የሥራ ቦታ ይዛወራል።

፭. ሁኔታው ሲያስገድድ አስተዳደሩ አንድን የማረሚያ ጥበቃ አባል ከፍ ያለ ደረጃ ባለው የሥራ መደብ ላይ በተጠባባቂነት እንዲሠራ ማድረግ ይችላል። ይህም ሲሆን አስተዳደሩ በሚወስነው መሠረት የተጠባባቂነት አበል ይከፈለዋል።

፮. አንድን የማረሚያ ጥበቃ አባል ከአንድ ዓመት በላይ በተጠባባቂነት ማሠራት አይቻልም።

፯. የአንድ ጥበቃ አባል የሥራ መደብ የተሰረዘ እንደሆነ በአስተዳደሩ ውስጥ ክፍት ሆኖ ወደሚገኝ ተመሳሳይ ደረጃ ወደአለው የሥራ መደብ እንዲዛወር ይደረጋል።

## ክፍል ሦስት
## የሥራ ሰዓት፣ ልዩ ልዩ ፈቃዶችና የሕክምና አገልግሎት

### ፲. መደበኛ የሥራ ሰዓት

፩. የጥበቃ አገልግሎት በቀን ፳፬ ሰዓት፣ በሳምንት ፯ ቀናትና በወር ፴ ቀናት በዓመት ፫፻፷፭/፫፻፷፮ ቀናት ያለማቋረጥ ይሰጣል።

፪. ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል መደበኛ የሥራ ሰዓት በቀን ፰ ሰዓት ሆኖ በሳምንት ከ፵ ሰዓት መብለጥ የለበትም። ሆኖም ለአስቸኳይ ጉዳይ ወይም ለልዩ የጥበቃ ሥራ የትርፍ ሰዓት ሥራ እንዲሰራ በአለቃው ከታዘዘ መሥራት ይኖርበታል። ለሰራበት ትርፍ ሰአት የማካካሻ ዕረፍት ይሰጠዋል።

### ፲፩. የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ዓላማ

፩. የዓመት ዕረፍት ፈቃድ የሚሰጠው የማረሚያ ጥበቃ አባል ለተወሰነ ጊዜ በማረፍ አገልግሎቱን በታደሰ መንፈስ እንዲቀጥል ለማስቻል ነው።

፪. የዓመት ዕረፍት ፈቃድ በገንዘብ አይለወጥም።

2. Any transfer to be made under sub-article (1) of this Article, shall be carried out on the basis of competition whenever there are prison wardens within the administration applying for the transfer.

3. Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, a prison warden may, without affecting his salary, be temporarily assigned to another position for not more than a year, irrespective of the grade or type of function to avoid any disruption in the activities of the Administration.

4. Where it is proved by a medical certificate that a prison warden is unable to carry out the functions of his position or to reside in his place of work due to his health condition, he shall be transferred to another suitable position or place of work with:

a) the same grade where such vacant position is available; or

b) a lower grade where a vacant position of the same grade is not available and he is willing to be transferred to a position of lower grade.

5. Where circumstances so require, a prison warden may be assigned to a higher position in an acting capacity and shall be entitled to acting allowance as determined by the Administration.

6. It is prohibited to assign a prison warden in an acting capacity for more than a year.

7. Where the position of a prison warden is abolished, he shall be transferred to another vacant position of an equal grade within the Administration.

## PART THREE
## WORKING HOURS, LEAVES AND MEDICAL SERVICES

### 10. Regular Working Hours

1. Custody service shall be continuously rendered for 24 hours a day, 7 days a week, 30 days a month and 365/366 days a year.

2. Regular working hours of any prison warden shall be 8 hours a day and shall not exceed 40 hours in a week; provided, however, that he shall be required to work for extra time when instructed by his immediate superior in time of emergency or for special warden duties. He shall be granted compensatory leave for the extra time he spent on duty.

### 11. Purpose of Annual Leave

1. The purpose of annual leave is to enable a prison warden get rest and resume work with renewed strength.

2. There shall be no payment in lieu of annual leave.

፫. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ድንጋጌ ቢኖርም የማረሚያ ጥበቃ አባሉ አገልግሎት መቋረጡ በሥራው ላይ ጉዳት የሚያደርስ መሆኑን አስተዳደሩ ሲያረጋግጥ ያልተወሰደው የዓመት ዕረፍት ፈቃድ በገንዘብ እንዲለወጥ ያደርጋል፡፡

፲፪. <u>የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ቀናት</u>

፩. አንድ ዓመት ያገለገለ የማረሚያ ጥበቃ አባል ፳ የሥራ ቀናት የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ያገኛል፡፡

፪. ከአንድ ዓመት በላ ያገለገለ የማረሚያ ጥበቃ አባል ለእያንዳንዱ ተጨማሪ ዓመት አንድ የሥራ ቀን እየታከለበት የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ያገኛል፡፡ ሆኖም የሚሰጠው የአንድ ዓመት ፈቃድ ከ፴ የሥራ ቀኖች መብለጥ የለበትም፡፡

፫. በሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ቀደም ሲል የተሰጠ አገልግሎት ለዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ አፈጻጸም የሚታሰብ ይሆናል፡፡

፲፫. <u>የዓመት ዕረፍት ፈቃድ አሰጣጥ</u>

፩. የዓመት ዕረፍት ፈቃድ የአስተዳደሩን ዕቅድ መሠረት በማድረግና በተቻለ መጠን የማረሚያ ጥበቃ አባሉን ፍላጎት በማመዛዘን በሚዘጋጅና የማረሚያ ጥበቃ አባሉ እንዲያውቀው በሚደረግ መርሃ ግብር መሠረት በበጀት ዓመት ውስጥ ይሰጣል፡፡

፪. አንድ የማረሚያ ጥበቃ አባል የዓመት ፈቃድ በሚወስድበት ጊዜ በዕረፍት ላይ የሚቆይበትን የአንድ ወር ደመወዙን በቅድሚያ ሊወስድ ይችላል፡፡

፫. ልዩ ሁኔታ ካላጋጠመ ወይም የማረሚያ ጥበቃ አባሉ ተከፋፍሎ እንዲሰጠው ጠይቆ የቅርብ አለቃው ካልፈቀደለት በቀር የዓመት ዕረፍት ፈቃድ አይከፋፈልም፡፡

፲፬. <u>የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ስለማስተላለፍ</u>

፩. የሥራው ሁኔታ በማስገደዱ ወይም በፀጥታ አለመረጋጋት ምክንያት የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ሊተላለፍ ይችላል፡፡

፪. የሥራው ሁኔታ በማስገደዱ ምክንያት የማረሚያ ጥበቃ አባል የዓመት ዕረፍት ፈቃዱ በበጀት ዓመቱ ውስጥ ሊሰጠው ያልቻለ እንደሆነ የማረሚያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ለሁለት የበጀት ዓመት ሊያስተላልፈው ይችላል፡፡ ሆኖም የጥበቃ አባሉ ያልተጠቀመበት የዓመት ዕረፍት ፈቃድ በሦስተኛው በጀት ዓመት መሰጠት አለበት፡፡

፲፭. <u>የወሊድ ፈቃድ</u>

፩. ነፍሰጡር የሆነች የማረሚያ ጥበቃ አባል፣

ሀ) ከእርግዝናዋ ጋር የተያያዘ ምርመራ ለማድረግ ሀኪም በሚያዘው መሠረት ደመወዝ የሚከፈልበት ፈቃድ ይሰጣታል፡፡

ለ) ከመውለዷ በፊት ዕረፍት እንድታደርግ ሀኪም ካዘዘ ደመወዝ የሚከፈልበት ዕረፍት ይሰጣታል፡፡

3. Notwithstanding the provisions of sub-article (2) of this Article, the Administration shall make payment for unused leave where it ascertains that the interruption of the service of the prison warden results in causing harm to the custody services.

12. *<u>Duration of Annual Leave</u>*

1. A prison warden shall be entitled to annual leave of 20 working days for his first year of service.
2. A prison warden having a service of more than a year shall be entitled to additional leave of one working day for every additional year of service; provided, however, that the duration of annual leave shall not exceed 30 working days.
3. Previous services rendered in any government office shall be considered for the application of sub-article 2 of this Article.

13. *<u>Granting of Annual Leave</u>*

1. Annual leave shall be granted within a budget year in accordance with a leave schedule made known to the prison wardens and prepared on the basis of due consideration of the interest of the Administration and, as much as possible, the preference of each prison warden.
2. A prison warden shall be entitled to advance payment of his monthly salary at the time of taking his annual leave.
3. Annual leave shall not be divided unless there is an exceptional circumstance or it is so requested by the prison warden and approved by his immediate superior.

14. *<u>Postponement of Annual Leave</u>*

1. Annual leave may be postponed due to compelling reasons of work or when security problems arise.
2. The head of a prison may authorize the postponement of annual leave for two budget years where, due to compelling reasons, it is difficult to grant a prison warden his annual leave within the same budget year; provided however, that the accumulated leave shall be granted within the third budget year.

15. *<u>Maternity Leave</u>*

1. A pregnant prison warden shall be entitled to:
   a) paid leave for medical examination in accordance with the recommendation of a doctor;
   b) paid leave before delivery if recommended by a doctor.

፪. ነፍሰጡር የሆነች የማረሚያ ጥበቃ አባል መውለጃዋ ሲደርስ እወልዳለሁ ብላ ከገመተችበት ቀን በፊት ሰላሳ ተከታታይ ቀናት የቅድመ ወሊድ ፈቃድ እንዲሁም ከወለደችበት ቀን ጀምሮ ስድሳ ተከታታይ ቀናት የወሊድ ፈቃድ ከደመወዝ ጋር ይሰጣታል፡፡

፫. የማረሚያ ጥበቃ አባል የወሰደችው የቅድመ ወሊድ ፈቃድ ሲያልቅ ያልወለደች እንደሆነ እስከምትወልድበት ቀን ድረስ ባሉት የሥራ ቀናት የምትቆይበት ዕረፍት በበጀት ዓመቱ ካላት የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ወይም በበጀት ዓመቱ የዓመት ዕረፍት ፈቃድ የሌላት እንደሆነ ከሚቀጥለው የበጀት ዓመት የዕረፍት ፈቃዷ መውሰድ ትችላለች፡፡

፬. የማረሚያ ጥበቃ አባል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተወሰነውን የወሊድ ፈቃድ ከጨረሰች በኋላ ብትታመም በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፮ በተደነገገው መሠረት የሕመም ፈቃድ መውሰድ ትችላለች፡፡

፲፮. የሕመም ፈቃድ

፩. ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል በሕመም ምክንያት ሥራ መሥራት ያልቻለ እንደሆነ የሕመም ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ለማረሚያ ጥበቃ አባል የሚሰጥ የሕመም ፈቃድ በተከታታይ ወይም በተለያየ ጊዜ ቢወሰድም ሕመሙ ከደረሰበት የመጀመሪያ ቀን አንስቶ ባለው የአሥራ ሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ከስምንት ወር ወይም በአራት ዓመት ውስጥ ከአሥራ ሁለት ወር አይበልጥም፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የሚሰጥ የሕመም ፈቃድ ለመጀመሪያዎቹ ሦስት ወራት ከሙሉ ደመወዝ ጋር፣ ለሚቀጥሉት ሦስት ወራት ከግማሽ ደመወዝ ጋር እና ለመጨረሻዎቹ ሁለት ወራት ያለደመወዝ ይሆናል፡፡

፬. ማንኛውም የጥበቃ አባል ሲታመም፣

ሀ) ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ካላጋጠመው በስተቀር በተቻለ ፍጥነት መታመሙን ለቅርብ አለቃው ማሳወቅ አለበት፡፡

ለ) በተከታታይ ከሦስት ቀን ወይም በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ ከስድስት ቀን በላይ በሕመሙ ምክንያት ከሥራ የቀረ እንደሆነ ለመታመሙ የሕክምና ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

፲፯. በሥራ ላይ ስለሚደርስ ጉዳት

፩. በሥራው ምክንያት ጉዳት የደረሰበት የማረሚያ ጥበቃ አባል የሚያስፈልገውን የሕክምና ወጪ አስተዳደሩ ይሸፍናል፡፡

፪. በሥራ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት የማረሚያ ጥበቃ አባል ከጉዳቱ ድኖ ወደ ሥራው እስኪመለስ ወይም በጉዳቱ ምክንያት ለዘለቄታው መሥራት ያልቻለ መሆኑ በሕክምና ማስረጃ እስኪረጋገጥ ድረስ የሕመም ፈቃድ ከሙሉ ደመወዝ ጋር ይሰጠዋል፡፡ ሆኖም የሚሰጠው የህመም ፈቃድ በማናቸውም ሁኔታ ከ፲፪ ወራት መብለጥ የለበትም፡፡

2. A pregnant prison warden shall be entitled to a period of 30 consecutive days of maternity leave with pay preceding presumed date of her confinement and a period of 60 consecutive days of maternity leave after her confinement.

3. If the pregnant prison warden does not deliver on the presumed date, the days subsequently taken before her confinement shall be replaced by the annual leave she is entitled to within the budget year or that of the following budget year if no annual leave is left.

4. The prison warden shall be entitled to sick leave in accordance with Article 16 of this Regulations, if she becomes sick after completion of her maternity leave under sub-article (2) of this Article.

16. *Sick Leave*

1. Any prison warden shall be entitled to sick leave where he is unable to work due to sickness.

2. The duration of sick leave to be granted to a prison warden in accordance with sub-article (1) of this Article shall not exceed 8 months in a year or 12 months in 4 years, whether counted consecutively or separately starting from the first day of his sickness.

3. Sick leave to be granted in accordance with sub-article (2) of this Article shall be with full pay for the first three months, with half pay for the next three months and without pay for the last 2 months.

4. Where any prison warden is absent from work due to sickness he shall:

a) notify his immediate superior, as soon as possible, unless prevented by force majore;

b) produce a medical certificate in case of absence for three consecutive days or for more than 6 days within a budget year.

17. *Employment Injury*

1. The Administration shall cover the necessary medical expenses incurred by a prison warden due to employment injury.

2. Any prison warden who has sustained an occupational injury shall be entitled to injury leave with pay until he recovers and resume work or until it is medically certified that he is permanently disabled; provided, however, that the leave so granted shall not exceed 12 months.

፫. የማረሚያ ጥበቃ አባሉ በአሥራ ሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ከጉዳቱ ድኖ ወደ ሥራ መመለስ ያለመቻሉ በሕክምና ማስረጃ ሲረጋገጥ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፭ የተደነገገው ጥቅም ይጠበቅለታል፡፡

፬. የማረሚያ ጥበቃ አባል ሕክምናውን በአግባቡ ባለመከታተሉ ወይም በሃኪም የተሰጠውን ትዕዛዝ ባለማክበሩ ሕክምናውን ያጓተተ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና (፪) መሠረት የሚሰጠው የሕክምና ጥቅምና ፈቃድ ይቋረጣል፡፡

፭. ከሥራ በመጣ ጉዳት ምክንያት ዘላቂ ሙሉ ወይም ከፊል የመሥራት ችሎታውን ያጣ የማረሚያ ጥበቃ አባል አግባብ ባለው የጡረታ ሕግ የተሰጠው መብት ይጠበቅለታል፡፡

፮. በደረሰበት ጉዳት ምክንያት የማረሚያ ጥበቃ አባሉ የሞተ እንደሆነ አግባብ ባለው የጡረታ ሕግ መሠረት የጡረታ አበል ለሕጋዊ ባለመብቶች ይከፈላል፡፡

፯. ለዚህ ደንብ ተፈጻሚነት ሲባል በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ማለት አግባብነት ባለው የአሠሪና የሰራተኛ ጉዳይ ሕግ የተሰጠውን ትርጓሜ ይይዛል፡፡

፲፰. የጋብቻ ፈቃድ

ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል ትዳር ሲይዝ ሦስት የሥራ ቀናት የጋብቻ ፈቃድ ከደመወዝ ጋር ይሰጠዋል፡፡

፲፱. የሐዘን ፈቃድ

፩. ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል የትዳር ጓደኛ፣ ተወላጅ፣ ወላጅ ወይም እስከ ሁለተኛ ደረጃ የሚቆጠር የሥጋ ወይም የጋብቻ ዘመድ የሞተበት እንደሆነ አባሉ የሚሄድበት ቦታ የደርሶ መልስ ቀናት ሳይጨምር ደመወዝ የሚከፈልበት የሦስት ተከታታይ ቀናት የሐዘን ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

፪. የማረሚያ ጥበቃ አባሉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተመለከቱት ውጭ የቅርብ ዘመድ ወይም ወዳጅ የሞተበት እንደሆነ አባሉ የሚሄድበት ቦታ የደርሶ መልስ ቀናትን ሳይጨምር ደመወዝ የሚከፈልበት የአንድ ቀን የሐዘን ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡ ሆኖም በዚህ ምክንያት የሚሰጥ የሐዘን ፈቃድ በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ ከስድስት ቀን መብለጥ የለበትም፡፡

፳. ከደመወዝ ጋር የሚሰጥ ልዩ ፈቃድ

ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል፣

፩. ከፍርድ ቤት ወይም ከሌሎች ሥልጣን ከተሰጣቸው አካላት መጥሪያ ሲደርሰው የተጠራበት ጉዳይ እስከሚያበቃበት ጊዜ ድረስ፣

፪. በሕዝብ ምርጫ ሥልጣን የሚይዙ የመንግሥት ኃላፊዎችን ለመምረጥ በምርጫው ለሚሳተፉ አባሎች ምርጫው ለሚወስድበት ጊዜ፣ ወይም

3. A prison warden who, as certified by a medical certificate, is unable to recover and resume work within 12 months shall be entitled to the benefits provided for under sub-article (5) of this Article.
4. Where the prison warden delays his recovery by not following the treatment properly or by his non-observance of doctor's instructions, his entitlement of the medical benefits and leave under sub-articles (1) and (2) of this Article shall cease.
5. A prison warden who has sustained permanent total or partial disability due to employment injury shall be entitled to benefits provided in the relevant pension law.
6. Where an employment injury resulted in the death of a prison warden, his survivals shall be entitled to survivors gratuity payable under the relevant pension law.
7. The definition given to the term "employment injury" under the relevant labor law shall be applicable with respect to the application of these Regulations.

18. *Marriage Leave*

Any prison warden shall be entitled to leave with pay for three working days when he concludes marriage.

19. *Mourning Leave*

1. Any prison warden shall be entitled to leave with pay for three consecutive days without including the time of the journey to and from the place, in the event of the death of his spouse, descendent, ascendant or any other relative up to the second degree, by consanguinity or affinity.
2. In the event of the death of his close relative or friend other than those specified in sub-article (1) of this Article, a prison warden shall be entitled to leave with pay for one day without including the time of the journey to and from the place.

20. *Special Leave with Pay*

Any prison warden shall be entitled to special leave with pay where:

1. he is summoned by a court or any other competent authority, for the time utilized for the same purpose;
2. he participates in the election of government officials, for the duration of the voting.

፫. በአስተዳደሩ ዕቅድ ወይም በግል ጥረቱ በተገኘው የትምህርት ዕድል በአገር ውስጥ ወይም በውጭ አገር እንዲማር አስተዳደሩ ሲወስንና የሚማረው ትምህርት ለሥራው አስፈላጊና ጠቃሚ መሆኑን አስተዳደሩ ሲያምንበት፣

ከደመወዝ ጋር ልዩ ፈቃድ ይሰጠዋል።

፳፩. ያለደመወዝ ስለሚሰጥ ፈቃድ

ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል በበቂ ምክንያት ደመወዝ የማይከፈልበት ልዩ ፈቃድ እንዲሰጠው ሲጠይቅና የማረሚያ ቤቱን ጥቅም የማይጎዳ ሲሆን የማረሚያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ሊፈቅድለት ይችላል።

፳፪. ስለህክምና አገልግሎት

፩. ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል በአስተዳደሩ የሕክምና ተቋም የሚሰጠውን ማንኛውንም የሕክምና አገልግሎት በነፃ የማግኘት መብት ይኖረዋል።

፪. የማረሚያ ጥበቃ አባሉ ሕመም ከአስተዳደሩ የሕክምና ተቋም አቅም በላይ ከሆነ በመንግሥት የሕክምና ተቋም እንዲታከም ይደረጋል።

፫. የማረሚያ ጥበቃ አባል የትዳር ጓደኛና አካለ መጠን ያልደረሱ ልጆቹ በአስተዳደሩና በመንግሥት ሕክምና ተቋሞች የሕክምና አገልግሎት በነጻ እንዲያገኙ ይደረጋል።

፬. የማረሚያ ጥበቃ አባል በዚህ ደንብ መሠረት ለሚያገኘው የሕክምና አገልግሎት የሚያደርገው የመዋጮ መጠን አስተዳደሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይፈፀማል።

፭. አስተዳደሩ በጡረታ የተገለሉ የማረሚያ ጥበቃ አባሎች የሕክምና አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

ክፍል አራት

የደመወዝ አከፋፈልና የጡረታ መብት

፳፫. ስለደመወዝና አበል

፩. ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል በመንግሥት በሚወሰነው መሠረት፣

ሀ) ለተመደበበት የሥራ ቦታ ደመወዝ ይከፈለዋል፣

ለ) እንደ አስፈላጊነቱ የሚወሰን ልዩ ልዩ አበል ሊከፈለው ይችላል።

፪. የጥበቃ አባል ደመወዝ ክፍያ የሚደረገው በየወሩ መጨረሻ ይሆናል።

፫. ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል የሁለት ወር ደመወዙን ለመበደር ይችላል። ሆኖም ብድሩን ከተበደረበት ጊዜ ጀምሮ በ፲፰ ወራት ውስጥ መክፈል ይኖርበታል ።

፳፬. ስለ ደመወዝ ስኬል

፩. አስተዳደሩ ለማረሚያ ጥበቃ አባሎች የሚያገለግል የደመወዝ ስኬል አጥንቶ ለሚመለከተው የበላይ አካል ያቀርባል። በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል።

፪. ደመወዝ ስኬሉም ለእያንዳንዱ የሥራ ደረጃ መነሻና መድረሻ ደመወዝ እንዲሁም በየጊዜው የሚደረገውን የደመወዝ ጭማሪ የሚያመለክቱ እርከኖች ይኖሩታል።

3. he gets educational opportunity at home or abroad according to the Administration's plan or through his personal effort and the Administration believes that the education is necessary and useful for his job.

21. Leave Without Pay

Where a prison warden, upon sufficient ground, applies for a special leave without pay, the head of the prison may authorize the grant of such leave if it does not adversely affect the interest of the Prison.

22. Medical Service

1. A prison warden shall have the right to get medical services, free of charge, in the Administration's medical institution.
2. Where the medical institution of the Administration is unable to treat the illness of the prison warden, he shall be treated in other government medical institutions.
3. The spouse and miner children of a prison warden shall have the right to get free medical service in the medical institution of the Administration and other government medical institutions.
4. The amount of contribution to be made by a prison warden for the medical benefits he gets under these Regulations shall be determined by Directives issued by the Administration.
5. The Administration shall facilitate the provision of medical services to retired prison wardens.

**PART FOUR**

**PAYMENT OF SALARY AND PENSION BENEFITS**

23. Salary and Allowances

1. Any prison warden shall, as determined by the Government, be paid.
   (a) a salary fixed for the position he is holding; and
   (b) various allowances that may be determined as the situation requires.
2. The salary of a prison warden shall be paid at the end of every month.
3. Any prison warden shall be entitled to borrow his two months salary; provided, however, that he shall pay it back within 18 months from the date of the loan.

24. Salary Scale

1. The Administration shall conduct and submit to the concerned higher organ studies on salary scales, applicable to prison wardens and implement same upon approval by the Council of Ministers.
2. The salary scales shall contain the minimum and maximum pay and steps indicating periodical increments for each grade.

፳፭. ስለ ደመወዝ ጭማሪ

፩. የማረሚያ ጥበቃ አባሎች ደመወዝ ጭማሪ የሚያገኙት በሥራ አፈጻጸም ምዘና ውጤት ላይ በመመሥረት ይሆናል።

፪. አጥጋቢና ከዚያ በላይ የሆነ የሥራ አፈፃፀም ውጤት ላገኙ የማረሚያ ጥበቃ አባሎች የሚሰጠው የደመወዝ ጭማሪ በየሁለት ዓመቱ ይሆናል።

፳፮. የደመወዝ ክፍያ ስለመያዝና ስለመቀነስ

፩. የማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል ደመወዝ ፣

ሀ/ በአባሉ ስምምነት፣

ለ/ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ፣ ወይም

ሐ/ በሕግ በተደነገገው መሠረት፣

ካልሆነ በስተቀር ሊያዝ ወይም ሊቀነስ አይችልም።

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ለ ወይም ሐ መሠረት ከማረሚያ ጥበቃ አባሉ ደመወዝ የሚቀነሰው ከደመወዙ አንድ ሦስተኛ መብለጥ የለበትም ።

፳፯. የጡረታ መብት

የማረሚያ ጥበቃ አባሎች የጡረታ መብት በመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ ቁጥር ፫፻፵፭/፲፱፻፺፭ ለፖሊስ አባሎች በተደነገገው መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል።

ክፍል አምስት

የጥበቃ አባሎች የመረጃ አያያዝ

፳፰. የግል ማህደር

፩. አስተዳደሩ ስለእያንዳንዱ የማረሚያ ጥበቃ አባል አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች የሚይዝ የግል ማህደር እንዲኖር ያደርጋል።

፪. ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል በግል ማህደሩ ውስጥ የሚገኙትን መረጃዎች የመመልከት ወይም ግልባጩን የመውሰድ መብት ይኖረዋል።

፫. ከሚመለከታቸው የአስተዳደሩ ሠራተኞች በስተቀር ዋና ዳይሬክተሩ ወይም ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ሳይፈቅድ ማንኛውም ሰው የአንድን የማረሚያ ጥበቃ አባል የግል ማህደር ማየት አይችልም።

፬. የማረሚያ ጥበቃ አባሉ ያላወቀውን ማንኛውንም ማስረጃ በግል ማህደሩ ውስጥ ማስቀመጥ የተከለከለ ነው።

፳፱. መረጃና የሥራ ልምድ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት

፩. የማረሚያ ጥበቃ አባል በግል ማህደሩ ውስጥ የሚገኝ መረጃ ለሦስተኛ ወገን እንዲገለጽለት ሲጠይቅ መረጃውን የሚገልጽ ደብዳቤ ይጻፍለታል።

፪. የማረሚያ ጥበቃ አባል በሥራ ላይ እያለ የሥራ ልምዱ ተጽፎ እንዲሰጠው ከጠየቀ እንዲሰጠው ይደረጋል።

፴. ስታትስቲካዊ መረጃዎች

አስተዳደሩ የማረሚያ ጥበቃ አባሎችን የሚመለከቱ ስታትስቲካዊ መረጃዎችን የመሰብሰብና የማጠናቀር ኃላፊነት አለበት።

፴፩. የሥራ አፈፃፀም ግምገማ

፩. የሥራ አፈፃፀም ግምገማ ዓላማ የማረሚያ ጥበቃ አባሎች፣

25. *Salary Increment*

1. periodical salary increments to be made to prison wardens shall be based on their performance evaluation results.
2. Prison wardens scoring satisfactory and above satisfactory performance evaluation results shall be entitled to salary increments every two years.

26. *Withholding and Deduction of Salary*

1. The salary of a prison warden may not be withheld or deducted except in accordance with:
   a) the consent of the prison warden;
   b) court order; or
   c) the operation of the law.
2. Monthly deductions from the salary of a prison warden to be made pursuant to Sub-Article 1 (b) or (c) of this Article, shall not exceed one third of his salary.

27. *Pension Benefits*

The pension benefits of prison wardens shall be effected in accordance with the provisions of the Public Servants' Pensions Proclamation No. 345/2003 applicable to members of the Police.

***PART FIVE***

***MANAGING INFORMATION PROFILE OF PRISON WARDENS***

28. *Personal Records*

1. The Administration shall keep personal records containing all relevant information regarding each prison warden.
2. Any prison warden shall have access to all information contained in his personal records or to have a copy thereof.
3. No person, other than the concerned administrative staff, shall have access to a prison warden's personal records unless authorized by the Director General or Deputy Director General of the Administration.
4. It is prohibited to deposit any document in the personal records of a prison warden without his knowledge.

29. *Issuing of Information Letter and Certificate of Work Experience*

1. A letter disclosing information in the personal file of a prison warden shall, upon his request, be issued to a third party.
2. A prison warden shall be issued with a certificate of work experience upon his request.

30. *Statistical Data*

The Administration shall have the duty to collect and compile statistical data regarding prison wardens.

31 *Performance Evaluation*.

1. The purpose of performance evaluation shall be to enable prison wardens to:

ሀ/ ሥራቸውን በሚጠበቀው መጠን በጥራት ደረጃና ጊዜ በተሟላ ሁኔታ እንዲያከናውኑ፣

ለ/ ጠንካራና ደካማ ጎናቸውን እንዲያውቁ፣ እና

ሐ/ የወደፊቱ የስራ አፈፃፀማቸው እንዲሻሻልና ለሥራ ያላቸውን ተነሳሽነት እንዲያጎለብቱ፣

ማስቻል ይሆናል።

፪. የሥራ አፈፃፀም ግምገማ በግልጽና ሥራው የሚመለከታቸው በተገኙበት በጋራ ይከናወናል።

፫. የሥራ አፈፃፀም ግምገማ አስተዳደሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይፈፀማል።

## ክፍል ስድስት

## የማረሚያ ጥበቃ አባሎች ግዴታዎችና ሥነ-ምግባር

፴፪. የማረሚያ ጥበቃ አባል ግዴታዎች

ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል፣

፩. ለሕገ-መንግሥቱና ለሕዝቡ ታማኝ የመሆን፣

፪. መላ ጉልበቱንና ችሎታውን ለሕዝብ አገልግሎት የማዋል፣

፫. በሥራ ዝርዝሩ ላይ የተሰጡትን ተግባሮችና ሌሎች በሕጋዊ መንገድ የሚሰጡ ትዕዛዞችን የመፈፀም፣ እና

፬. አስተዳደሩ የሚያወጣቸውን መመሪያዎች ሁሉ የማክበር፣

ግዴታ ይኖርበታል።

፴፫. ስለኃይል አጠቃቀም

፩. በማረሚያ ጥበቃ አባል የሚደረግ የኃይል አጠቃቀም በሕግ የተደገፈና ሕጋዊ ሥልጣንን መሠረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል።

፪. ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል፣

ሀ/ ታራሚዎችን በሚጠብቅ አባል ወይም በሌሎች ታራሚዎች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ለማድረስ ሲሞከር፣

ለ/ ታራሚዎች በማረሚያ ቤት ክልል ውስጥና ከማረሚያ ቤት ክልል ውጪ ታጅበው በሚሄዱባቸው ቦታዎች በአድማ ወይም በተናጠል የማምለጥና የማስመለጥ ሙከራ ሲደረግ፣

ሐ/ ከውስጥና ከውጪ የሚሰነዘር ጥቃትን ለመከላከል፣

ተመጣጣኝ ኃይል ሊጠቀም ይችላል።

፴፬. ስለጥበቃ አባል ሥነ-ምግባር

ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል ለዚህ ደንብ ድንጋጌዎችና አስተዳደሩ ለሚያወጣቸው የሥነ-ምግባር መመሪያዎች ተገዥ መሆን አለበት።

፴፭. ታዛዥነት

ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል ፣

፩. ሥራውን ባለው ዕውቀትና ችሎታ ሙሉ ለሙሉ በመጠቀም መፈፀም አለበት፤

፪. የተመደበበትን መደበኛ ሥራና ሌላውንም ተመሳሳይ ሥራ የመፈፀም ግዴታ አለበት፤

፫. በወንጀል ሕግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከበላይ ኃላፊው የሚሰጠውን ትዕዛዝ መፈፀም አለበት።

፴፮. ሚስጥር ስለመጠበቅ

ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል፣

a) effectively discharge their duties in accordance with the expected level, quality standards and time.

b) identify their strengths and weakness; and

c) improve their future performances and develop self initiative.

2. Performance evaluation shall be transparent and shall be carried out with the collective participation of the concerned working groups.

3. Performance evaluations shall be carried out in accordance with directives issued by the Administration.

## PART SIX

## DUTIES AND ETHICS OF PRISON WARDENS

32. *Duties of Prison Wardens*

Any prison warden shall:

1. be faithful to the Constitution and the people;
2. devote his whole energy and capacity to provide public service;
3. carryout all functions specified in his job description and other lawful orders given to him;
4. respect all directives issued by the Administration.

33. *Use of Force*

1. Any use of force by a prison warden shall be supported by law and based on legal authority.
2. Any prison warden may use reasonable force where:
   (a) there is an attempt to cause serious harm on a prison warden guarding prisoners or on other prisoners in custody;
   (b) there is an attempt, either individually or in group, to escape or to assist in escaping of prisoners within a prison or outside of a prison while being accompanied.
   (c) there is an attack launched from within or outside of the prison.

34. *Ethical Conduct of Prison Wardens*

Any prison warden shall adhere to the provisions of this Regulations and directives issued by the Administration on the ethical conduct of prison wardens.

35. *Obedience*

Any prison wardens shall:

1. perform his duties to his best knowledge and ability;
2. discharge the usual duties of his position as well as other similar duties.
3. without prejudice to the provisions of the Criminal Code, obey the orders of his superior.

36. *Secrecy*

Any prison warden may not :

፩. አግባብነት ባለው ሕግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሀገርንና የሕዝብን ደህንነት የሚጎዱ ሚስጥር የተባሉ መረጃዎችን ለማንኛውም ሰው አሳልፎ መስጠት የለበትም፤

፪. ሥልጣን ባለው ኃላፊ ካልታዘዘ ወይም በሥራ ላይም ሆነ ከሥራው ውጪ ጉዳዩን እንዲያውቀው የሚገባው ሰው ካልሆነ በቀር በአሰራር ሚስጥር የሆኑትን መረጃዎች ለማናቸውም ሰው መግለጽ የለበትም።

፴፯. ገንዘብ ስለመበደርና ስጦታ ስለመቀበል

፩. የማረሚያ ጥበቃ አባል በሚሰጠው አገልግሎት ምክንያት ከማንኛውም ሰው ገንዘብ መበደር የለበትም።

፪. ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል ከሥራው ጋር በተያያዘ ሁኔታ ስለሰጠው ወይም ስለሚሰጠው አገልግሎት ከማናቸውም ሰው ስጦታ ወይም ዋጋ መጠየቅ ወይም መቀበል የለበትም።

፴፰. ገቢን ስለማሳወቅ

የማረሚያ ጥበቃ አባል ከደመወዝ ውጭ የሚያገኘውን ገቢ ለአስተዳደሩ ማሳወቅ አለበት።

፴፱. ስለጥቅም ግጭቶች

፩. ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል ከራሱ ወይም ከዘመዱ ወይም ከወዳጁ ጥቅም ጋር የተያያዘና ከሥራ ኃላፊነቱ ጋር ግጭት የሚፈጠርበት ጉዳይ ሲያጋጥመው ለአለቃው በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት።

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተጠቀሰው ሁኔታ ሲያጋጥም ጉዳዩ የተገለፀለት ኃላፊ የማረሚያ ጥበቃ አባሉ የጥቅም ግጭቱን ለማስወገድ በሚችል መልክ ሥራውን እንዲያከናውን ማድረግ ይኖርበታል።

፫. ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል ሥራውን ሲያከናውን ለማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት አድሎ ማድረግ ወይም ወገንተኝነት ማሳየት የለበትም ።

፵. ሌላ ስራ መሥራት ስለሚከለከልበት ሁኔታ

፩. ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል ለመሥሪያ ቤቱ የሚሰጠውን አገልግሎት የሚያጓድል ወይም በማንኛውም አኳኋን ከተመደበበት ሥራ ጋር የሚቃረን ወይም ከጥበቃ አባልነቱ ጋር የማይጣጣም ማናቸውንም ሌላ ሥራ መሥራት የለበትም።

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል ለመሥሪያ ቤቱ አሳውቆ በትርፍ ጊዜው ማናቸውንም ሌላ ሥራ ለመሥራት ይችላል።

፵፩. ስለንብረት አያያዝና አጠቃቀም

ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል ለሥራው ማከናወኛ የተሰጡትን መሣሪያዎችና መገልገያዎች በአግባቡ የመጠበቅና የመጠቀም ኃላፊነት አለበት።

፵፪. በዕዳ ስለመጠየቅ

ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል ለሥራው ማከናወኛ በተሰጡት መሣሪያዎችና መገልገያዎች ላይ ለሚደርስ ጉዳት ወይም ጥፋት በዕዳ ተጠያቂ የሚሆነው ጉዳቱ ወይም ጥፋቱ በእርሱ ቸልተኝነት ወይም ሆን ተብሎ በተፈፀመ ድርጊት ምክንያት የደረሰ እንደሆነ ነው።

1. without prejudice to the provisions of the relevant laws, disclose to any person classified information that might endanger the security of the State and the public.
2. disclose information that has been considered secret to any person unless such person is officially permitted access to the information or unless he is ordered by the concerned superior.

37. *Borrowing Money and Accepting Gifts*

1. A prison warden may not borrow money in connection with the service he renders.
2. Any prison warden shall not demand or accept any gift or payment in return for service rendered or expected to be rendered by him.

38. *Declaration of Income*

Any prison warden shall declare to the Administration all his income other than his salary.

39. *Conflict of Interest*

1. Any prison warden shall report in writing to his superior the case in which a conflict of interest between his private interests or that of his relative or friend and his duties has arisen.
2. The superior, to whom the case referred to in Sub-Article (1) of this Article is reported, shall take appropriate measures to resolve the conflict of interest in order to accomplish the task.
3. Any prison warden, while executing his duty, shall not favor or show partiality to a political organization.

40. *Prohibition of Holding other Jobs*

1. Any prison warden shall not engage in any other job which might impair his services or be in conflict with his duties or inconsistent with his position as prison warden.
2. Without prejudice to the provisions of Sub-Article (1) of this Article, a prison warden may, after informing the Administration, engage in any other work during his leisure time.

41. *Handling and Use of Property*

Any prison warden shall have the responsibility to properly handle and use equipment and materials provided to carry out his duties.

42. *Extent of Liability*

Any prison warden shall be liable for the damage or loss of equipment and materials provided to him to carry out his duties, where such damage or loss is caused by his negligence or intentional act.

፵፫. <u>የደንብ ልብስ የመልበስ ግዴታ</u>

ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል በሥራ ላይ ሲሆን የደንብ ልብሱን አሟልቶ መልበስ ይኖርበታል፡፡

፵፬. <u>ንጽህና ስለመጠበቅ</u>

ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል የግል ንጽህናውንና የደንብ ልብሱን ንጽህና በሚገባ መጠበቅ አለበት፡፡

፵፭. <u>ስለሌሎች ግዴታዎች</u>

ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል፣

፩. የደንብ ልብሱንና የጦር መሣሪያ ለማንኛውም ሰው ማዋስ፣ መሸጥ፣ መለወጥ ወይም ማስያዝ፣

፪. የሚመለከተው ኃላፊ ሳይፈቅድ ማንኛውንም ዓይነት የእርዳታ መዋጮ ማሰባሰብ፣

፫. ከጋብቻ ቀለበት በስተቀር የደንብ ልብሱን ሲለብስ ጌጣጌጥ ማድረግ፣

፬. ሠላማዊ ሰልፍና የሥራ ማቆም አድማ ማድረግ፣

የለበትም፡፡

## <u>ክፍል ሰባት</u>

## <u>አገልግሎት ማቋረጥና ማራዘም</u>

፵፮. <u>በገዛ ፈቃድ አገልግሎት ስለማቋረጥ</u>

፩. ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል የሰባት ዓመት አገልግሎቱን ከፈፀመ በኋላ የአንድ ወር ቅድሚያ የጽሑፍ ማስታወቂያ በመስጠት ሥራውን በገዛ ፈቃዱ ሊለቅ ይችላል፡፡

፪. የማረሚያ ጥበቃ አባሉ ለሥራው እጅግ አስፈላጊና በቀላሉ ለመተካት የማይቻል ሆኖ ሲገኝ አስተዳደሩ የመልቀቂያ ጥያቄውን ከሦስት ወር ለማይበልጥ ጊዜ ሊያራዝመው ይችላል፡፡

፫. የማረሚያ ጥበቃ አባሉ መልቀቂያውን የጠየቀው የግዴታ አገልግሎት ዘመኑን ሳያጠናቅቅ ወይም ልዩ ሥልጠና ወስዶ የሚያስፈልገውን አገልግሎት ያላጠናቀቀ ከሆነ አስተዳደሩ ለእርሱ ሥልጠና ያወጣውን ማናቸውንም ወጪ መክፈል ይኖርበታል፡፡

፬. ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፫) ከተደነገገው ውጪ በገዛ ፈቃዱ አገልግሎቱን ያቋረጠ እንደሆነ በኮብላይነት ተመዝግቦ የፖሊስ አባላትን በሚመለከት ተፈጻሚነት ባላቸው የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ክስ እንዲመሰረትበት ይደረጋል፡፡

፵፯. <u>በሕመም ወይም በሥራ በመጣ ጉዳት ምክንያት ለአገልግሎት ብቁ ስለአለመሆን</u>

፩. ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፮(፪) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ወደ ሥራ ለመመለስ ካልቻለ የሕክምና ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልግ በሕመም ምክንያት ለሥራው ብቁ እንዳልሆነ ተቆጥሮ አገልግሎቱ እንዲቋረጥ ይደረጋል፡፡

43. *Duty to Wear Uniform*

Any prison warden shall wear his complete uniforms while executing his duty.

44. <u>*Hygiene*</u>

Any prison warden shall have the responsibility to properly maintain personal hygiene and neatness of his uniform.

45. <u>*Other Obligations*</u>

Any prison warden shall not:

1. lend, sell, exchange or pledge his uniform and fire arms to any other person;
2. collect any contribution for aid without the permission of the concerned official;
3. wear any jewelry while wearing uniforms other than a marriage ring;
4. engage in any strike and demonstration.

## <u>*PART SEVEN*</u>

## <u>*TERMINATION AND EXTENSION OF SERVICE*</u>

46. <u>*Resignation*</u>

1. Any prison warden who has completed his seven years of services may resign at any time upon giving a one-month written notice.
2. Where the service of the prison warden is indispensable and he could not be replaced easily, the Administration may delay his release for a period not exceeding three months.
3. A prison warden who has applied for resignation prior to completing the period of his obligatory service or who has received special training and has not rendered the required service shall reimburse the Administration the expenses incurred for his training.
4. Any prison warden who terminates his service without observing the provisions of sub-Articles (1) - (3) of this Article shall be considered as a deserter and be subjected to criminal charges in accordance with the provisions of the Criminal Code applicable with respect to members of the Police.

47. <u>*Unfitness Due to Illness and Occupational Injury*</u>

1. Where a prison warden is unable to resume work within the time specified under Article 16 (2) of these Regulations, he shall with no requirement of a medical certificate, be deemed unfit for service and be discharged.

፪. የዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ ፪ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በሥራው ምክንያት ጉዳት የደረሰበት የማረሚያ ጥበቃ አባል ለዘለቄታው መሥራት አለመቻሉ በሕክምና ማስረጃ ሲረጋገጥ ወዲያውኑ ከሥራ እንዲሰናበት ይደረጋል፡፡

፵፰. <u>በችሎታ ማነስ ምክንያት ከሥራ ስለማሰናበት</u>

፩. ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል ያለውን እውቀትና ችሎታ ተጠቅሞ የተመደበበትን ሥራ ለመስራት የተቻለውን ጥረት እያደረገ የሥራ አፈፃፀም ውጤቱ በተከታታይ በሁለት ጊዜ ከመካከለኛ ነጥብ በታች ከሆነ ከሥራ እንዲሰናበት ይደረጋል፡፡

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ቀደም ባሉት ተከታታይ አምስት ዓመታት ከፍተኛ የሥራ አፈፃፀም ውጤት ሲያገኝ የነበረ የማረሚያ ጥበቃ አባል የሥራ አፈፃፀም ውጤት በተከታታይ ለሦስት ጊዜ ከመካከለኛ ነጥብ በታች ካልሆነ በስተቀር ከሥራ አይሰናበትም፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ወይም ፪ መሠረት አንድን የማረሚያ ጥበቃ አባል ከሥራ ማሰናበት የሚቻለው፣

ሀ) ለያዘው የሥራ መደብ የሚያስፈልገውን ሥልጠና በመስጠት ፣ ወይም

ለ) ከያዘው የሥራ ደረጃ ጋር ተመሳሳይ በሆነና ሊሰራው ወደሚችለው ሌላ የሥራ መደብ በማዛወር ፣

እንዲሰራ ከተደረገ በኋላ የጥበቃ አባሉ የሥራ አፈፃፀም ውጤቱን ለማሻሻል ያልቻለ እንደሆነ የአንድ ወር ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ይሆናል ፡፡

፵፱. <u>በዲስፕሊን ምክንያት ከሥራ ስለማሰናበት</u>

፩. ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል ፣

(ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ከሥራ እንዲሰናበት የዲስፕሊን ቅጣት የተወሰነበት ፣ እና

(ለ) በዚህ ደንብ መሠረት ይግባኝ ብሎ ቅጣቱ ያልተሰረዘለት ፣

እንደሆነ አገልግሎቱ ይቋረጣል ፡፡

፪. የማረሚያ ጥበቃ አባሉ የተላለፈበት የዲስፕሊን ውሳኔ በይግባኝ ከተሻሻለለት ወይም ከተሰረዘለት በክርክር ወቅት ሳይከፈለው የቀረው ደመወዝ ታስቦ ያለወለድ ይከፈለዋል፡፡

፶. <u>በዕድሜ ምክንያት አገልግሎት ስለማቋረጥ</u>

፩. ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል አገልግሎቱ ካልተራዘመ በስተቀር በሕግ ከተወሰነው የጡረታ ዕድሜ ከደረሰበት የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ያለተጨማሪ ሥነ-ሥርዓት አገልግሎቱ እንዲቋረጥ ይደረጋል፡፡

፪. የማረሚያ ጥበቃ አባሉ ጡረታ ከመውጣቱ ከሦስት ወር በፊት በጽሑፍ እንዲያውቀው መደረግ አለበት፡፡

2. Without prejudice to the provisions of Article 17 (2) of these Regulations, where a prison warden who has sustained employment injury is medically determined to be permanently disabled his service shall forthwith be terminated.

48. *<u>Termination on Grounds of Inefficiency</u>*

1. The service of a prison warden may be terminated where his performance evaluation results are unsatisfactory for two successive evaluation periods despite exerting all his knowledge and ability to accomplish his work.
2. Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, a prison warden whose performance evaluation results are above satisfactory in the preceding five successive years may not be dismissed on grounds of inefficiency unless his performance results becomes unsatisfactory for the following three successive evaluation periods.
3. the termination of service of a prison warden under Sub-Article (1) or (2) of this Article shall only be effected upon giving him a one month prior notice where he is unable to improve his performance after :
   a) receiving a training required for his position; or
   b) being transferred to another suitable position of an equal grade.

49. *<u>Termination on Disciplinary Grounds</u>*

1. The service of a prison warden shall be terminated where:
   a) disciplinary penalty under sub-article (1) of Article 55 of these Regulations is imposed on him; and
   b) the penalty is not cancelled on appeal made under these Regulations.
2. Where the penalty is mitigated or cancelled on appeal the prison warden shall be entitled to, with out interest, the payment of his salary withheld during the appeal.

50. *<u>Retirement</u>*

1. Unless a prison warden is retained in service beyond the retirement age, his service shall be terminated without any additional formality on the last day of the last month in which he attained the retirement age determined by law.
2. the prison warden shall be notified of his retirement in writing three months prior to his retirement.

፶፩. የአገልግት የምስክር ወረቀት

ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል በማናቸውም ምክንያት አገልግሎቱን ሲያቋርጥ ሲያከናውን የነበረውን የሥራ ዓነት ፣ የአገልግሎት ዘመኑን፣ ሲከፈለው የነበረውን ደመወዝና ከሥራ የተሰናበተበትን ምክንያት የሚገልጽ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል ፡፡

፶፪. የአገልግሎት ጊዜ ሲቋረጥ ስለሚፈፀም ክፍያ

፩. ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል አገልግሎቱን በሚያቋርጥበት ጊዜ የሠራበት ደመወዝና አበል ይከፈለዋል፡፡

፪. አግባብ ባለው የጡረታ ሕግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ የማረሚያ ጥበቃ አባል በሞት ምክንያት አገልግሎቱ ሲቋረጥ በሕይወት ሳለ ለአስተዳደሩ በጽሑፍ ላሳወቃቸው የትዳር ጓደኛ ወይም በስሩ ይተዳደሩ ለነበሩ ቤተሰቦች በአንድ ጊዜ የሦስት ወር ደመወዝ ይከፈላል፡፡

፶፫. የአገልግት ጊዜ ስለማራዘም

፩. አንድ የማረሚያ ጥበቃ አባል የጡረታ ዕድሜው ከደረሰ በኋላ በአንድ ጊዜ እስከ ሁለት ዓመት በጠቅላላው ከአምስት ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ አገልግሎቱን ማራዘም ይቻላል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የማረሚያ ጥበቃ አባል አገልግሎትን ማራዘም የሚቻለው፣

(ሀ) የማረሚያ ጥበቃ አባሉ ትምህርት ፣ ልዩ ዕውቀትና ችሎታ ለሚሠራው ሥራ ጠቃሚ ሆኖ ሲገኝ፣

(ለ) ተተኪ የማረሚያ ጥበቃ አባል ለማግኘት አለመቻሉ ሲረጋገጥ፣

(ሐ) የማረሚያ ጥበቃ አባሉ ለሥራው ብቁ መሆኑ በሕክምና ማስረጃ ሲረጋገጥ፣

(መ) የማረሚያ ጥበቃ አባሉ አገልግሎቱን ለመቀጠል ሲስማማ ፣ እና

(ሠ) የአገልግሎቱን መራዘም አስተዳደሩ ሲፈቅድ፣

ይሆናል ፡፡

ክፍል ስምንተ

ስለ ዲሲፕሊን

፶፬. የዲስፕሊን ቅጣት ዓላማ

የዲስፕሊን ቅጣት ዓላማ የማረሚያ ጥበቃ አባል በፈፀመው የዲስፕሊን ጉድለት ተፀጽቶ እንዲታረምና ሥራውን በአግባቡ እንዲያከናውን ለማስቻል ወይም የማይታረም ሆኖ ሲገኝ ለማሰናበት ነው፡፡

፶፭. የዲስፕሊን ቅጣት ዓይነቶች አመዳደብ

፩. የዲስፕሊን ጉድለት የፈፀመ የማረሚያ ጥበቃ አባል እንደጥፋቱ ክብደት ከሚከተሉት አንዱ ሊወሰንበት ይችላል፡፡

ሀ) የቃል ማስጠንቀቂያ ፤

ለ) የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ፤

ሐ) የጉልበት ሥራና ወታደራዊ ቅጣት፤

መ) እስከ አንድ ወር ደመወዝ የሚደርስ መቀጫ፤

51. Certificate of Service

Where the service of a prison warden is terminated for any reason or where he so requests, he shall be provided with a certificate of service indicating the type and duration of his service, his salary and the reason for the termination.

52. Severance Pay

1. Any prison warden shall, upon termination of his service, be paid his earned salary and allowances.
2. Without prejudice to the provisions of the relevant pension law, where the service of a prison warden is terminated due to his death, an amount equivalent to his three months' salary shall be paid to his spouse or dependents who have been made known to the Administration in writing.

53. Extension of Service

1. The service of a prison warden may be extended beyond his retirement age for a period up to two years at a time and for a period not exceeding five years in total.
2. The service of a prison warden may be extended under sub-article (1) of this Article where:
   a) His qualification, special skill and ability is found to be essential;
   b) It is proved that it is impossible to replace him by another prison warden;
   c) He is proved fit for service by medical certificate;
   d) He has agreed to the extension of his service; and
   e) The extension of the service is approved by the Administration.

**PART EIGHT**

**DISCIPLINE**

54. Objectives of Disciplinary Penalties

The objectives of disciplinary penalty shall be to rehabilitate a delinquent prison warden when he can learn from his mistakes and become a reliable prison warden or to discharge him when he becomes recalcitrant.

55. Types and classification of Disciplinary Penalties

3. Depending on the gravity of the offence, one of the following penalties may be imposed on a prison warden for breach of discipline:
   a) Oral warning;
   b) Written warning;
   c) Physical work and military punishment ;
   d) Fine up to one month's salary;

ሠ) እስከ ሦስት ወር ደመወዝ የሚደርስ መቀጫ፤

ረ) ከሥራ ደረጃና ደመወዝ ዝቅ ማድረግ ፤

ሰ) ከሥራ ማሰናበት፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (ሐ) የተዘረዘሩት ቀላል የዲስፕሊን ቅጣቶች ፣ ከፊደል ተራ (መ) እስከ (ሰ) የተዘረዘሩት ከባድ የዲሰፕሊን ቅጣቶች ተብለው ይመደባሉ።

፶፮. <u>ቀላል የዲስፕሊን ቅጣት የሚያስከትሉት ጥፋቶች</u>

የሚከተሉት ጥፋቶች ቀላል የዲስፕሊን ቅጣት ሊያስከትሉ ይችላሉ፤

፩. በሥራ ላይ የተሟላ የደንብ ልብስ ለብሶ አለመገኘት፤

፪. ያስበቂ ምክንያት ወይም ያለፈቃድ ከሥራ መቅረት፤

፫. በሥራ ቦታ ተገኝቶ ወደ ሥራ አለመሰማራት፤

፬. በሥራ ሰዓት ተሰብስቦ ማውራት ፤

፭. የሥነ-ሥርዓት ጉድለቶችን ለሚመለከተው ክፍል አለማሳወቅ፤

፮. ንጽሕናን ያለመጠበቅ፤

፯. በዚህ አንቀጽ ከተዘረዘሩት ተመሳሳይ ክብደት ያለውን ማንኛውንም የዲስፕሊን ጉድለት መፈፀም ።

፶፯. <u>ከባድ የዲስፕሊን ቅጣት የሚያስከትሉ ጥፋቶች</u>

የሚከተሉት ጥፋቶች ከባድ የዲስፕሊን ቅጣት ሊያስከትሉ ይችላሉ፤

፩. በሕገ-መንግሥቱ የተደነገጉትን ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች መጣስ፤

፪. ትዕዛዝ ባለማክበር ፣ በቸልተኝነት፣ በመለገም ወይም የአሠራር ሥነ- ሥርዓትን ባለመከተል በሥራ ላይ በደል ማድረስ፤

፫. ከግዳጅ ላይ መሸሽ፤

፬. ሥራ እንዳይሰራ ሆነ ብሎ ማወክ ወይም ከሚያውኩት ጋር መተባበር ፤

፭. ከማንኛውም ፍርድ ቤት የሚሰጥ ትዕዛዝን አለማክበር፤

፮. በቀላል የዲስፕሊን ቅጣት እርምጃዎች ባለመታረም ያለበቂ ምክንያት በተደጋጋሚ ከሥራ መቅረት ወይም የሥራ ሰዓት አለማክበር፤

፯. በሥራ ቦታ በጠብ አጫሪነት መደባደብ፤

፰. በስካር ወይም በአደንዛዥ እፅ ሱስ በመመረዝ ሥራን መበደል ፤

፱. ጉቦ መቀበል ወይም እንዲሰጠው መጠየቅ ፤

፲. በሥራ ቦታ ወይም የደንብ ልብሱን እንደለበሰ ከሥራ ቦታ ውጭ ለሕዝብ ሞራል ተቃራኒ የሆነ ድርጊት መፈፀም፤

፲፩. የሌብነት ወይም የእምነት ማጉደል ድርጊት መፈፀም፤

፲፪. በአስተዳደሩ ንብረት ላይ ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት ጉዳት ማድረስ ፤

(e) Fine up to three month's salary;

(f) Down grading;

(g) Dismissal.

2 The penalties specified under paragraphs (a) – (c) of sub-article (1) of this Article shall be classified as simple disciplinary penalties, and those specified under paragraphs (d) – (g) shall be classified as rigorous penalties.

56. <u>*Offences Entailing Simple Penalties*</u>

Simple disciplinary penalties may be imposed for the following offences:

1. Failure to wear a complete uniform while on duty ;
2. Absence from duty without good cause or without permission;
3. Failure to actively engage on duty while present at work place;
4. Engaging in idle group talk while on duty;
5. Failure to notify a breach of discipline to the concerned authority;
6. Failure to keep one's hygiene;
7. Committing any breach of discipline of equal gravity with the offences specified under this Article.

57. <u>*Offences Entailing rigorous Penalties*</u>

Rigorous disciplinary penalties may be imposed for the following offences:

1. Violation of human and democratic rights stipulated in the constitution;
2. Impair once duty by being disobedient negligent or tardy or non-observance of working procedures;
3. To run away from duty;
4. To deliberately obstruct work or to collaborate with others in committing such offence;
5. Failure to observe any court orders;
6. Unjustified repeated absence or non-observance of office hours in spite of being penalized by simple disciplinary penalties;
7. To engage in physical violence at the place of work;
8. To neglect duty by being alcoholic or drug addict;
9. To accept or demand bribe;
10. To commit an immoral act at the place of work or outside of work while wearing his uniform;
11. To commit an act of theft or breach of trust;
12. To inflict damages to the property of the Administration due to an intentional act or negligence;

፲፫. በሥልጣን አላግባብ መጠቀም ፤

፲፬. ምሥጢር የሆኑ መረጃዎችን አለመጠበቅ፤

፲፭. ታራሚን ማስመለጥ ፤ እንዲያመልጥ መፍቀድ ወይም መርዳት ፤

፲፮. ለታራሚዎችም ሆነ ለሕዝብ ደህንነት ተገቢውን እርዳታ ያለማድረግ፤

፲፯. የተከለከሉ ዕቃዎችን ወደ ማረሚያ ቤቱ ማስገባት ወይም እንዲገባ ድጋፍ መስጠት ፤

፲፰. የታራሚዎችን ሰብዓዊ መብት መርገጥ፤

፲፱. በሕገ-ወጥ ድርጊት ከታራሚዎች ጋር መመሳጠር ፤

፳. ከታራሚ ወይም በማረሚያ ቅጥር ግቢ ውስጥ ከሌላ ማንኛውም ሰው ጋር የዝሙት ተግባር መፈጸም ፤

፳፩. ለመስሪያ ቤቱ የሚሰጠውን አገልግሎት የሚያጓድል ወይም በማንኛውም አኳኋን ከተመደበበት ሥራ ጋር የሚቃረን ወይም ከጥበቃ አገልግሎቱ ጋር የማይጣጣም ማንኛውንም ሌላ ሥራ መሥራት፤

፳፪. ታራሚ ወደ ማረሚያ ቤት ሲገባ ያስቀመጠውን ንብረት በጊዜው ያለመመዝገብ ወይም እንዲመዘገብ ያለማድረግ ፣ እንዲበላሽ ማድረግ ፣ለግል ጥቅም ማዋል ፣ መደበቅ ወይም ማጥፋ ፤

፳፫. የታራሚን የፍትህ ጉዳይ በአግባቡና በዕለቱ ተከታትሎ ያለመፈጸም፤

፳፬. በዚህ አንቀጽ ከተዘረዘሩት ጋር ተመሳሳይ ክብደት ያለው ሌላ የዲስፕሊን ጉድለት መፈጸም፡፡

፶፰. <u>ስለዲስፕሊን እርምጃ አወሳሰድ</u>

፩. በማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል ላይ የዲስፕሊን ቅጣት ከመወሰኑ በፊት ፈፀመ የተባለውን የዲስፕሊን ጉድለት በጽሑፍ እንዲያውቀው ተደርጎ ራሱን የመከላከል ዕድል ይሰጠዋል ፤

፪. ከባድ የዲስፕሊን ጥፋት የሚታየው በዲስፕሊን ኮሚቴው ሆኖ የኮሚቴው የውሳኔ ሐሳብ ለአስተዳደሩ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ቀርቦ ውሳኔ ይሰጥበታል፡፡

፫. ቀላል የዲስፕሊን ቅጣት ውሳኔ የሚሰጠው የዲስፕሊን ጥፋት በፈጸመው የማረሚያ ጥበቃ አባል የቅርብ አለቃው ይሆናል፡፡

፬. የዲስፕሊን ቅጣት ማንኛውንም የፍርድ ቤት ውሳኔ ሳይጠብቅ ወይም ሳይከተል ሊወሰን ይችላል፡፡

፶፱. <u>ከሥራ ስለማገድ</u>

፩. የማረሚያ ጥበቃ አባል በወንጀል ወይም በዲስፕሊን ጥፋት የተከሰሰ እንደሆነና ድርጊቱ ከሥራው የሚያስወጣው መሆኑ ሲገመት አስተዳደሩ ከሥራና ደመወዙ ታግዶ እንዲቆይ ያደርጋል፡፡

፪. የማረሚያ ጥበቃ አባል ከሥራ ታግዶ መቆየት ለአስተዳደሩ ሥራ አፈፃፀም ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ከሁለት ወር ለማይበልጥ ጊዜ ከሥራና ደመወዝ ታግዶ እንዲቆይ ማድረግ ይችላል፡፡

13. To abuse power;
14. To reveal information classified as secret;
15. To allow or assist a prisoner to escape;
16. Failure to provide necessary support to prisoners or the public;
17. To bring or provide support in bringing prohibited items into a prison;
18. Violate the human rights of prisoners ;
19. To conspire with prisoners in unlawful activities;
20. To commit with a prisoner or with any other person sexual intercourse within the premises of the prison ;
21. To engage in any other job which might impair his services or be in conflict with his duties or inconsistent with his position as prison warden;
22. Failure to register or cause the timely registration of the property of a prisoner deposited at the time when he is admitted into a prison or to damage, use for personal benefit, hide or cause the loss of such property;
23. failure to properly follow up and execute daily judicial cases of prisoners;
24. To commit any breach of discipline of equal gravity with the offences specified under this Article.

58. *<u>Taking Disciplinary Measures</u>*

1. Before imposing a disciplinary penalty on any prison warden, he shall be informed of the alleged offence in writing and be given the opportunity to defend himself;
2. Disciplinary offenses entailing rigorous penalties shall be investigated by a disciplinary committee, and the recommendation of the committee shall be submitted for the decision of the Deputy Director General of the Administration.
3. A disciplinary measure shall be taken by the immediate superior of a prison warden who has committed a disciplinary offence entailing simple disciplinary penalties.
4. Disciplinary measures may be taken irrespective of any court proceedings or action.

59. *<u>Suspension from Duty</u>*

1. A prison warden shall be suspended from duty and his salary shall be withheld if he is charged with a criminal or disciplinary offence for which his dismissal is to be expected.
2. A prison warden may be suspended from duty by withholding his salary for a period not exceeding two months if that course of action is necessary in the interest of discharging the duties of the Administration.

፷. ስለይግባኝ

፩. ቀላል የዲስፕሊን ቅጣት ውሳኔ የተወሰነበት ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል በውሳኔው ቅር ከተሰኘ ውሳኔውን ከሰጠው የቅርብ ኃላፊው አንድ ደረጃ ከፍ ለሚለው ኃላፊ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል። ይግባኝ የቀረበለት ኃላፊ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል ።

፪. ከባድ የዲስፕሊን ቅጣት ውሳኔ የተወሰነበት ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል ለአስተዳደሩ ዋና ዳይሬክተር ይግባኝ ማቅረብ ይችላል። በዋና ዳይሬክተሩ የሚሰጠው ውሳኔም የመጨረሻ ይሆናል።

፷፩. ስለይርጋ ጊዜ

፩. ቀላል የዲስፕሊን ቅጣት የሚያስከትል ጥፋት የፈፀመ የጥበቃ አባል የፈፀመው ጥፋት ከታወቀበት ቀን ጀምሮ እስከ ስድስት ወር እርምጃ ካልተወሰደበት በዲስፕሊን ተጠያቂ አይሆንም ።

፪. በወንጀል ጭምር የሚያስጠይቅ ከባድ የዲስ ፕሊን ቅጣት የሚያስከትል ጥፋት የፈጸመ የማረሚያ ጥበቃ አባል የወንጀሉን ክስ ለማቅረብ በወንጀል ሕጉ በተደነገገው የይርጋ ጊዜ ውስጥ በዲስፕሊን ካልተከሰሰ በጥፋቱ ተጠያቂ አይሆንም ።

፫. በወንጀል የማያስጠይቅ ከባድ የዲስፕሊን ቅጣት የሚያስከትል ጥፋት የፈጸመ የማረሚያ ጥበቃ አባል የደንብ መተላለፍ ክስን ለማቅረብ በወ ንጀል ሕጉ በተደነገገው የይርጋ ጊዜ ውስጥ በዲስፕሊን ካልተከሰሰ በጥፋቱ ተጠያቂ አይሆንም ።

፬. የሚመለከተው ኃላፊ፣

ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ የዲስፕሊን እርምጃ ሳይወስድ ወይም ክስ ሳያቀርብ ከቀረ ፣ ወይም

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደ ነገገው የዲስፕሊን ክስ ማቅረቢያ የይርጋ ጊዜ ቢኖርም በዚሁ ንዑስ አንቀጽ የተገለጸውን ክስ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ካላቀረበ ፣

ተጠያቂ ይሆናል ።

## ክፍል ዘጠኝ

## በወንጀል ስለተከሰሰ የማረሚያ ጥበቃ አባል

፷፪. ከሥራው ጋር በተገናኘ ሁኔታ በወንጀል ስለተከሰሰ የማረሚያ ጥበቃ አባል

የማረሚያ ጥበቃ አባል የተከሰሰበትን የወንጀል ድርጊት የፈፀመው የሥራ ግዴታውን ሲወጣ በነበሩት ሁኔታዎች አስገዳጅነት መሆኑን የአስተዳደሩ አመራር ጉባዔ ሲያረጋግጥ ፣ ጉዳዩ በዲስፕሊን ግድፈት የሚያስከትለው ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ ፣

፩. የአስተዳደሩ ነገረፈጅ በክሱ ሂደት ወክሎት ይከራከርለታል ፤

፪. የዋስ መብቱ ተከብሮለት ከተለቀቀ በሥራው ላይ ሆኖ ሙሉ ደመወዙ ይከፈለዋል ፤

60. Right of Appeal

1. A prison warden may appeal against a decision on simple disciplinary measures to his next higher superior. The decision of such superior shall be final.
2. A prison warden may appeal against a decision on rigorous disciplinary penalties to the Director General of the Administration . The decision of the Director General shall be final.

61. Period of Limitation

1. Disciplinary measure may not be taken against a prison warden who has committed an offence entailing simple disciplinary penalty unless such measure is taken within six months from the time the breach of discipline is known.
2. No disciplinary charge may be brought against a prison warden who has committed an offense entailing rigorous disciplinary penalty, as well as criminal liability, unless such charge is brought within the time limit provided for in the Criminal Code for the criminal charge.
3. No disciplinary charge may be brought against a prison warden who has committed an offense entailing rigorous disciplinary penalty, and not subject to criminal liability, unless such charge is brought within the time limit provided for in the criminal Code for instituting charges involving petty offences.
4. The concerned official shall be held responsible if he has failed:
   a) To take or institute the disciplinary measures or charges within the time limit specified under sub-article (1) or (2) of this Article; or
   b) Notwithstanding the time limit provided for under sub-article (2) of this Article, to institute the disciplinary charge specified therein within one year.

## PART NINE

## PRISON WARDENS ACCUSED OF CRIMES

62. Crime Related to Prison Warden's Duties

Where the Administration's management council is convinced that a crime a prison warden is accused of was committed due to a compelling circumstance prevailed while he was discharging his duties, and without prejudice to disciplinary measures that may be taken against him:

1. he shall be represented by the attorney of the Administration in the criminal proceeding;
2. he shall be retained in service and receive his full salary if he is released on bail;

፫. የዋስ መብቱ ሳይከበርለት ቀርቶ የሚታሰር ከሆነ፣ ጉዳዩ በፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚሰጥበት ጊዜ ድረስ ሙሉ ደመወዙ ይከፈለዋል ፤
፬. በተከሰሰበት ወንጀል ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛነቱን አረጋግጦ የቅጣት ውሳኔ ካስተላለፈበት ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ከሥራ ይሰናበታል ፤
፭. ከሦስት ዓመት ባልበለጠ ጊዜ የእስራት ቅጣት ተፈርዶበት እስራቱን ጨርሶ እንደወጣ እስከ አንድ ወር ጊዜ ቀርቦ ሲያመለክት ጉዳዩ በኮሚቴ ተጣርቶ ወደ ሥራው እንዲመለስ ሊደረግ ይችላል።

፷፫. ከሥራው ጋር ባልተገናኘ ሁኔታ በወንጀል ስለተከሰሰ የማረሚያ ጥበቃ አባል

ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል ከሥራው ጋር ግንኙነት በሌለው ሁኔታ በፈጸመው ድርጊት ክስ ከቀረበበት፣ ጉዳዩ በዲስፕሊን ግድፈት የሚያስከትለው ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣

፩. የተከሰሰው በደንብ መተላለፍ ጥፋት ሆኖ በዋስ ከተለቀቀ በሥራው ላይ ሆኖ ደመወዙን እያገኘ ይከራከራል፤
፪. የተከሰሰው በወንጀል ከሆነ ከሥራና ደመወዝ ታግዶ እንዲቆይ ይደረጋል፤
፫. በተከሰሰበት ወንጀል ፍርድ ቤት በነፃ ካሰናበተውና እስከ አንድ ወር ጊዜ ቀርቦ ሲያመለክት ጉዳዩ በኮሚቴ ተጣርቶ ወደ ሥራው እንዲመለስ ሊደረግ ይችላል፤ ሆኖም ከሥራው ታግዶ ለቆየበት ጊዜ ደመወዝ አይከፈለውም፤
፬. በተከሰሰበት ወንጀል ፍርድ ቤት በነፃ ካሰናበተውና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ወደ ሥራው እንዲመለስ ከተደረገ በኋላ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ጉዳዩ ታይቶ በጥፋተኛነት ቅጣት ከተወሰነበት ከሥራው ይሰናበታል።

## ክፍል አሥር
## ማዕረግ፣ የደረጃ ዕድገትና ሽልማት

፷፬. ስለማዕረግ

የማረሚያ ጥበቃ አባላት የማዕረግ ተዋረድና ስያሜ እንደሚከተለው ይሆናል።

፩. ዋርደር፤
፪. ረዳት ሰርጀንት፤
፫. ምክትል ሰርጀንት፤
፬. ሰርጀንት፤
፭. ዋና ሰርጀንት፤
፮. ረዳት ኦፊሰር፤
፯. ምክትል ኦፊሰር፤
፰. ኦፊሰር፤
፱. ዋና ኦፊሰር፤
፲. ሱፐርኢንተንደንት፤
፲፩. ዋና ሱፐርኢንተንደንት፤
፲፪. ዳይሬክተር፤
፲፫. ምክትል ዋና ዳይሬክተር፤
፲፬. ዋና ዳይሬክተር።

፷፭. የማዕረግ እርከኖች

የማረሚያ ጥበቃ አባላት የማዕረግ አሰጣጥ በሚከተሉት እርከኖች የተከፈለ ይሆናል፤

፩. የመጀመሪያ ማዕረግ እርከን፤
  ሀ) ዋርደር፤
  ለ) ረዳት ሰርጀንት፤
  ሐ) ምክትል ሰርጀንት፤
  መ) ሰርጀንት፤
  ሠ) ዋና ሰርጀንት፤
፪. የመካከለኛ ማዕረግ እርከን፤
  ሀ) ረዳት ኦፊሰር፤
  ለ) ምክትል ኦፊሰር፤
  ሐ) ኦፊሰር፤

3. If he is not released on bail, he shall be paid his full salary until the court renders final decision;
4. Where the court convicted and penalized him, he shall be dismissed from his work as of the date of such decision;
5. Where he is sentenced to imprisonment for not more that three years and has submitted his application within one month from the date of his release, he may be reinstated to his job after the case has been inquired by a committee.

63. *Crimes unrelated to Prison Warden's Duties*

Without prejudice to any disciplinary measure that may be taken against him. Where a prison warden, due to an act unrelated with his duties:

1. Is accused of committing a petty offence and is released on bail by the court, he shall follow up his case while remaining on his duty and receiving his salary;
2. Is accused of committing a crime, he shall be suspended from his duty and his salary shall be withheld;
3. Is accused of committing a crime and is acquitted by the court, he may be reinstated to his job after the case has been inquired by a committee; provided, however, that he shall not be entitled to any payment of salary for the period of suspension;
4. Convicted and penalized by an appellate court subsequent to his acquittal and reinstatement pursuant to sub-article (3) of this Article, he shall be dismissed from his duty.

## PART TEN
## RANK, PROMOTION AND PRIZE

64. RANK

Hierarchy and designation of ranks of prison wardens shall be:

1. warden;
2. Assistant Sergeant;
3. Deputy Sergeant;
4. Sergeant;
5. Chief Sergeant;
6. Assistant Officer;
7. Deputy Officer;
8. Officer;
9. Chief Officer;
10. Superintendent;
11. Chief Superintendent;
12. Director;
13. Deputy Director General;
14. Director General.

65. *Rank Levels*

The ranks of prison wardens shall be classified into the following levels:

1. lower rank level:
   a) warden;
   b) Assistant sergeant;
   c) Deputy Sergeant;
   d) Sergeant;
   e) Chief Sergeant;
2. Medium rank level:
   a) Assistant Officer;
   b) Deputy Officer;
   c) Officer;

፫. የከፍተኛ ማዕረግ እርከን፤
ሀ) ዋና ኦፊሰር፤
ለ) ሱፐርኢንተንደንት፤
ሐ) ዋና ሱፐርኢንተንደንት፤
መ) ዳይሬክተር፤
ሠ) ምክትል ዋና ዳይሬክተር፤
ረ) ዋና ዳይሬክተር፡፡

፷፮. <u>የማዕረግ ምልክት</u>

፩. ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል ከደንብ ልብሱ ጋር የሚደረግ የማዕረግ ምልክት ያደርጋል፡፡
፪. የማዕረግ ምልክቶቹ አሠራርና የቀለም ዓይነት የማዕረግ እርከኖችን ለመለየት የሚያስችል ይሆናል፡፡

፷፯. <u>ስለማዕረግ ዕድገት</u>

፩. ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል የማዕረግ እድገት ከማግኘቱ በፊት በያዘው ማዕረግ ለሚከተለው ጊዜ መቆየት አለበት ፤

| ተ.ቁ | የተያዘው ማዕረግ | የቆይታ ጊዜ | | በዕድገት የሚገኘው ማዕረግ |
|---|---|---|---|---|
| | | ለመደበኛ ዕድገት | ለተፋጠነ ዕድገት | |
| 1 | ዋርደር | 4 ዓመት | 3 ዓመት | ረዳት ሰርጀንት |
| 2 | ረዳት ሰርጀንት | 3 ዓመት | 2 ዓመት | ምክትል ሰርጀንት |
| 3 | ምክትል ሰርጀንት | 3 ዓመት | 2 ዓመት | ሰርጀንት |
| 4 | ሰርጀንት | 3 ዓመት | 2 ዓመት | ዋና ሰርጀንት |
| 5 | ዋና ሰርጀንት | 3 ዓመት | 2 ዓመት | ረዳት ኦፊሰር |
| 6 | ረዳት ኦፊሰር | 2 ዓመት | 1 ዓመት | ምክትል ኦፊሰር |
| 7 | ምክትል ኦፊሰር | 3 ዓመት | 2 ዓመት | ኦፊሰር |
| 8 | ኦፊሰር | 3 ዓመት | 2 ዓመት | ዋና ኦፊሰር |
| 9 | ዋና ኦፊሰር | 3 ዓመት | 2 ዓመት | ሱፐር ኢንተንደንት |
| 10 | ሱፐር ኢንተንደንት | 3 ዓመት | 2 ዓመት | ዋና ሱፐር ኢንተንደንት |
| 11 | ዋና ሱፐር ኢንተንደንት | 3 ዓመት | 2 ዓመት | ዳይሬክተር |

፪. ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል፤
ሀ) ሊሾም የሚችልበት ክፍት የማዕረግ እርከን ሲኖር፤
ለ) ለሚሾምበት ክፍት የማዕረግ እርከን የሚያስፈልገው የትምህርት ደረጃ፣ የሥራ ልምድና የሥራ አፈጻጸም ሲኖረው፣ እና
ሐ) ለማዕረግ እርከኑ የሚሰጠውን ሥልጠና ካጠናቀቀ፣
ለማዕረግ ዕድገት ብቁ ይሆናል፡፡

፫. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የማዕረግ ዕድገት የሚሠጠው በውድድርና በፈተና ይሆናል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ለረዳት ኦፊሰር የሚያበቃው የመቆያ ጊዜ ቢኖርም የአስተዳደሩ የትምህርት ወይም የሥልጠና ተቋም የሚያወጣውን መመዘኛ የሚያሟላ በመጀመሪያ ደረጃ የማዕረግ እርከን ላይ የሚገኝ የማረሚያ ጥበቃ አባል ለረዳት ኦፊሰርነት መወዳደር ይችላል፡፡

፭. ከፍ ያለ ሥራ የፈፀመ ወይም የላቀ የሥራ ችሎታ ያሳየ የማረሚያ ጥበቃ አባል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ለተፋጠነ የማዕረግ ዕድገት ብቁ ሊሆን ይችላል፡፡

3. higher rank level;
   a) Chief Officer;
   b) Superintendent;
   c) Chief Superintendent;
   d) Director;
   e) Deputy Director General;
   f) Director General.

66. *<u>Rank Insignia</u>*

1. Any prison warden shall wear, with his uniform, a rank insignia;
2. The type and color of rank insignia shall enable to differentiate rank levels.

67. *<u>Promotion</u>*

1. A prison warden holding a given rank shall serve for the following period of time to be promoted to the next higher rank:

| No. | Current rank | Period of Service | | Next Higher Rank |
|---|---|---|---|---|
| | | Regular Promotion | Accelerated Promotion | |
| 1 | Warden | 4 years | 3 years | Assistant Sergeant |
| 2 | Assistant Sergeant | 3 years | 2 years | Deputy Sergeant |
| 3 | Deputy Sergeant | 3 years | 2 years | Sergeant |
| 4 | Sergeant | 3 years | 2 years | Chief Sergeant |
| 5 | Chief Sergeant | 3 years | 2 years | Assistant Officer |
| 6 | Assistant Officer | 2 years | 1 years | Deputy Officer |
| 7 | Deputy Officer | 3 years | 2 years | Officer |
| 8 | Officer | 3 years | 2 years | Chief Officer |
| 9 | Chief Officer | 3 years | 2 years | Superintendent |
| 10 | Superintendent | 3 years | 2 years | Chief Superintendent |
| 11 | Chief Superintendent | 3 years | 2 years | Director |

2. A prison warden shall be eligible for promotion where:
   (a) There is a vacant position for appointment;
   (b) He fulfils the educational, work experience and efficiency requirements of the vacancy;
   (c) He has completed the training required for the rank.
3. Without prejudice to the provisions of sub-article (2) of this Article, a promotion to any level of rank shall be carried out on the basis of competition and examination.
4. Notwithstanding the period of service required for the rank of assistant officer in accordance with sub-article (1) of this Article, a prison warden in a lower rank level shall be entitled to compete for the rank of assistant officer if he fulfills the requirements set by the educational or training center of the Administration.
5. A prison warden who has made commendable contribution in his work or who has scored outstanding performance may be eligible for an accelerated promotion in accordance with sub-article (1) of this Article.

፮. ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል ከሥራው ጋር ግንኙነት ባለው መስክ እውቅና ካለው የትምህርት ተቋም ተጨማሪ ትምህርት ወስዶ ከተመረቀ የትምህርት ማስረጃው ለማዕረግ ዕድገት ግምት ውስጥ ይገባለታል፡፡

፯. ከባድ የዲስፕሊን ቅጣት የተላለፈበት የማረሚያ ጥበቃ አባል ቅጣቱ ከተጣለበት ቀን ጀምሮ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ለማዕረግ ዕድገት መወዳደር አይችልም፡፡

፰. የማዕረግ ዕድገት ያገኘ የማረሚያ ጥበቃ አባል ለአደገበት ማእረግ የተወሰነውን መነሻ ደመወዝ ያገኛል፤ ሆኖም ዕድገት ከማግኘቱ በፊት ያገኝ የነበረው ደመወዝ ዕድገት ካገኘበት ማዕረግ መነሻ ደመወዝ በላይ ወይም እኩል የሆነ እንደሆነ ቀጥሎ ያለውን የአዲሱን ማዕረግ የዕርከን ደመወዝ ያገኛል፡፡

፷፰. ሽልማት

አስተዳደሩ የላቀ የሥራ ውጤት ለሚያስመዘግቡ የማረሚያ ጥበቃ አባላት በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ሽልማት ሊሰጥ ይችላል፡፡

## ክፍል አሥራ አንድ
## ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች

፷፱. የዲስፕሊን ኮሚቴ መቋቋም

፩. ከባድ የዲስፕሊን ቅጣት የሚያስከትሉ ጥፋቶችን የመመርመርና የውሳኔ ሃሳብ የማቅረብ ሥልጣን የተሰጠው የአስተዳደሩ የዲስፕሊን ኮሚቴ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪. የዲስፕሊን ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለአስተዳደሩ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ይሆናል፡፡

፸. የዲስፕሊን ኮሚቴ አባላት

፩. የዲስፕሊን ኮሚቴው ሰብሳቢና ሦስት አባላቱ በአስተዳደሩ የሚመደቡና አንዱ በጥበቃ አባላት የሚመረጥ ሆኖ ቢያንስ አንድ አባል ሴት የማረሚያ ጥበቃ አባል መሆን አለበት፡፡

፪. የዲስፕሊን ኮሚቴው ፀሐፊ በአስተዳደሩ ይመደባል፡፡

፫. የዲስፕሊን ኮሚቴው አባላት የሥራ ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል፡፡

፸፩. የዲስፕሊን ኮሚቴ የአሠራር ሥርዓት

የዲስፕሊን ኮሚቴው የራሱን የአሠራር ሥርዓት መመሪያ አዘጋጅቶ ለአስተዳደሩ ያቀርባል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

፸፪. የእድገት ኮሚቴ መቋቋም

የማረሚያ ጥበቃ አባላትን የማዕረግ ዕድገት መርምሮ ለአስተዳደሩ የውሳኔ ሃሳብ የሚያቀርብ የዕድገት ኮሚቴ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፸፫. የእድገት ኮሚቴው አባላት

፩. የእድገት ኮሚቴው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፤

ሀ) አስተዳደሩ የሚመድበው ከፍተኛ መኮንን.......ሰብሳቢ

6. Where a prison warden takes additional training related to his profession from a recognized educational institution, such educational achievement shall be taken into consideration for his promotion.

7. A prison warden on whom a rigorous disciplinary penalty is imposed may not be eligible for promotion within two years from the date of the penalty.

8. When a prison warden is promoted, he shall be entitled to the starting salary of the new grade; provided, however, that where his salary before his promotion was more than or equal to the starting salary of the new grade, his new salary shall be the next higher step of the new grade.

68. *Awarding of Prizes*

The Administration may, in accordance with directives it issues, award prizes to prison wardens to acknowledge their outstanding accomplishments.

## PART ELEVEN
## VARIOUS COMMITTEES

69. *Establishment of Disciplinary Committee*

1. The Disciplinary Committee of the Administration is hereby established to examine disciplinary charges entailing rigorous penalties and to submit recommendations.
2. The disciplinary committee shall be accountable to the Deputy Director General of the Administration.

70. *Members of the Disciplinary Committee*

1. the chairperson and three members of the Disciplinary Committee shall be assigned by the Administration and one member shall be elected by prison wardens. At least one of the members shall be a female prison warden.
2. The Secretary of the Disciplinary Committee shall be assigned by the Administration.
3. The term of office of members of the Disciplinary Committee shall be two years.

71. *Rules of Procedures of the Disciplinary Committee*

The Disciplinary committee shall prepare and submit its rules of procedure to the Administration and implement same upon approval.

72. *Establishment of Promotion Committee*

The Promotion committee of the Administration is hereby established to examine the promotion of prison wardens and to submit recommendations.

73. *Members of the Promotion Committee*

1. The Promotion Committee shall have the following members:
   a) A senior officer assigned by the Administration..................Chairperson

ለ) የማረሚያ ጥበቃ አባላት አስተዳደር ኃላፊ፣ ክፍት የሥራ መደቡ የሚገኝበት የሥራ ክፍል ኃላፊ እና በአስተዳደሩ የሚመደቡ ሌሎች ሁለት የማረሚያ ጥበቃ አባ ላት.........አባላት

ሐ) ሁለት የማረሚያ ጥበቃ አባላት ተወካ ዮች...........................አባላት

፪. የእድገት ኮሚቴው በአስተዳደሩ የሚመደብ ጸሐፊ ይኖረዋል፡፡

፫. ከእድገት ኮሚቴው አባላት መካከል ቢያንስ አንድ አባል ሴት የማረሚያ ጥበቃ አባል መሆን አለባት፡፡

፬. ለዕድገት ኮሚቴው የሚመረጡት አባላት በሥነ-ምግባራቸው፣ በፍትሐዊነታቸውና በሥራ አፈጻጸም ብቃታቸው የተመሰገኑ ሆነው በአስተዳደሩ ውስጥ ከ፭ ዓመት በላይ ያገለገሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

፭. የዕድገት ኮሚቴው አባላት የሥራ ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል፡፡

፸፬. የእድገት ኮሚቴው ኃላፊነት

፩. የዕድገት ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለአስተዳደሩ ዋና ዳይሬክተር ሆኖ፤

ሀ) የተወዳዳሪዎች ምዝገባ በወጣው ማስታወቂያ መሠረት በትክክልና በተሟላ ሁኔታ መከናወኑን ያረጋግጣል፡፡

ለ) የተወዳዳሪዎችን የትምህርትና የሥራ ልምድ ማስረጃ ትክክለኛነት ይመረም ራል፡፡

ሐ) ለደረጃ እድገት የቀረቡትን ተወዳዳሪዎች በመመዘኛው መሠረት አወዳድሮ በደረጃ ያስቀምጣል፤

መ) በውድድሩ ውጤት መሠረት የውሳኔ ሃሳቡን ያቀርባል፤

፪. የደረጃ ዕድገት ኮሚቴው ተወዳዳሪዎችን በመምረጥ ሂደት የማጣራት ሥራ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ማንኛውንም የአስተዳደሩን የሥራ ክፍል ማነጋገር ይችላል፡፡

፸፭. የእድገት ኮሚቴው የአሠራር ሥርዓት

፩. በማናቸውም የዕድገት ኮሚቴው ስብሰባ ከአባ ላቱ ከ፪/፫ኛው ያላነሱ ሲገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

፪. ማናቸውም የዕድገት ኮሚቴው ውሳኔ በድምጽ ብልጫ ያልፋል፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል ከተከፈለ የኮሚቴው ሰብሳቢ የደገፈው ሀሳብ የኮሚቴው ውሳኔ ይሆናል፡፡

፫. ኮሚቴው በድምጽ ብልጫ በሚወስንበት ጊዜ ሁሉ የአነስተኛ ድምጽ አስተያየት ከነምክንያቱ በስብሰባው ቃለ ጉባኤ መመዝገብ አለበት፡፡

፬. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የዕድገት ኮሚቴው የራሱን የአሠራር ሥርዓት መመሪያ አዘጋጅቶ ለአስተዳደሩ ያቀርባል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፡፤

፸፮. የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ስለማቋቋም

አስተዳደሩ የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ያቋቁማል፣ ተግባርና የአሠራር ሥርዓቱን በመመሪያ ይወስናል፡፡

b) The head of personnel administration, the head of the department where the vacant position is available and two other prison wardens to be assigned by the Administration..................members

c) Two representatives of prison wardens.................................members

2. The Secretary of the Promotion committee shall be assigned by the Administration.

3. At least one of the members of the Promotion committee shall be a female prison warden.

4. Members of the Promotion Committee shall be selected from prison wardens honored for their discipline, fairness and work efficiency and have served for at least Five Years in the Administration.

5. The term of office of the Promotion Committee shall be two years.

74. *Responsibilities of the promotion committee*

1. The Promotion committee shall be accountable to the Director General of the Administration and shall:

a) ensure that the registration of candidates has been carried out properly and exhaustively in accordance with the notice issued;

b) examine the genuineness of the credentials of candidates;

c) Conduct the selection of candidates in accordance with the selection criteria and list them in order of their results;

d) submit its recommendations on the basis of the results of the selection.

2. The Promotion Committee may, where it finds it necessary in the course of selecting candidates for promotion, inquire any department of the Administration for relevant information.

75. *Rules of Procedures of the Promotion Committee*

1. The presence of not less than 2/3 of the members of the Promotion Committee at any meeting shall constitute quorum;

2. Any decision of the Promotion Committee shall be passed by a majority vote; in case of a tie, the chairperson shall have a casting vote.

3. When a decision of the Committee is passed by majority vote, the opinions of the minority shall, with the reasons thereof, be recorded in the minutes.

4. Without prejudice to the provisions of this Article, the Committee may formulate, and submit to the Administration, its own rules of procedures and implement same upon approval.

76. *Establishment of Grievance Committee*

The Administration shall establish a grievance hearing committee and determine, by directives, its functions and rules of procedures.

## ክፍል አሥራ ሁለት
## ትጥቅ፣ ዓርማና መታወቂያ

**፸፯. ስለ ትጥቅና የደንብ ልብስ ዕደላ**

ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል የሚያገኘው ትጥቅና የደንብ ልብስ በአስተዳደሩ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

**፸፰. ስለዓርማው ይዘት**

፩. የአስተዳደሩ ዓርማ ለሕግ ተገዥነትን፣ ሰላምን፣ ሰብዓዊነትን፣ ሙያንና አስተማሪነትን የሚያንፀባርቅ ይሆናል፡፡

፪. የዓርማው ቀለም ውሃ ሰማያዊና ነጭ ይሆናል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

**፸፱. ስለዓርማው አጠቃቀም**

የአስተዳደሩ ዓርማ በመለዮ፣ በመታወቂያ ካርድ፣ በደንብ ልብስና አስተዳደሩ እንደአስፈላጊነቱ በሚወስነው ቦታ ላይ ሊደረግ ይችላል፡፡

**፹. ስለመታወቂያና መለያ ቁጥር**

፩. ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል በአስተዳደሩ የተሰጠ መታወቂያና መለያ ቁጥር ይኖረዋል፡፡

፪. የመታወቂያ ካርዱ የአስተዳደሩን ዓርማ የያዘ ሆኖ፣

ሀ) የማረሚያ ጥበቃ የአባሉን ሙሉ ስም፣ ማዕረግ፣ የሥራ ኃላፊነት፣ መለያ ቁጥር፣ የደም ዓይነት፣ እና

ለ) በአደጋ ጊዜ ተጠሪ የሚሆን ሰውን ስምና አድራሻ፣ የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡

፫. ማንኛውም የጥበቃ አባል መደበኛ ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ መታወቂያ ካርዱን ማሳየት ይኖርበታል፡፡

## ክፍል አሥራ ሦስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፹፩. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

አስተዳደሩ ይህን ደንብ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ማውጣት ይችላል፡፡

**፹፪. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ደንቦችና መመሪያዎች**

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ደንብ ወይም መመሪያ በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**፹፫. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሐምሌ ፯ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

## PART TWELVE
## EQUIPMENT, EMBLEM AND IDENTITY CARD

77. *Distribution of Equipment and Uniform*

The equipment and uniform to be provided for any prison warden shall be determined by directives to be issued by the Administration.

78. *Content of Emblem*

1. The emblem of the Administration shall reflect obedience to the law, peace, humanity and professionalism and shall be educative.
2. The color of the emblem shall be light blue and white. The details shall be determined by directives.

79. *Use of Emblem*

The emblem of the Administration may be used on warden caps, identity cards and uniforms and on any place determined by the Administration as may be necessary.

80. *Identity cards and Identification Numbers*

1. Any prison warden shall have identity card and identification number issued by the Administration.
2. The identity card shall bear the emblem of the Administration and show:
   a) the full name, rank, work position, identification number and blood type of the prison warden; and
   b) the name and address of a person to be called in case of emergency.
3. Any prison warden shall, while performing his regular duty, show his identity card.

## PART THIRTEEN
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

81. *Power to Issue Directives*

The Administration shall have the power to issue directives necessary for the proper implementation of these Regulations.

82. *Inapplicable Regulations and Directives*.

No regulations or directives shall, in so far as they are inconsistent with these Regulations, be applicable with respect to matters covered by these Regulations.

83. *Effective Date*

These Regulations shall come into force on the date of their publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 14th day of July 2007.

**MELES ZENAWI**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE